ሊቀ ዲያቆናት

# ሀቢብ ጊዮርጊስ

እና

ሥራዎቹ

ጸሐፊ :- ሚካኤል ገብርኤል
**የእንግሊዝኛው ትርጉም**:- ሻዊር ኮብሩን
ተርጓሚ :- ዲያቆን ሄኖክ ኃይሌ

**የመጻሕፍቱ የእንግሊዘኛ ርዕስ ፡- Archdeacon Habeeb Guirguis**
**Mystery of Godliness** /የተመረጡ ጽሑፎች/

© ማኅበረ ቅዱሳን
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው!

**ይህ መጽሐፍ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን ኤዲቶሪያል ቦርድ ታርሞና ተስተካክሎ የተፈቀደ ነው።**

ዲያቆን ሄኖክ ኃይሌ
251 091 2 08 18 29
24467 / 1000 አዲስ አበባ
Email : **henok_tshafi@yahoo.com**

**የሽፋን ገጽ ቅንብር** ፡- **ምሥራቅ ተፈራ**

# መታሰቢያነቱ

በየጉባኤ ቤቱ ፣ በመንፈሳዊ ኮሌጆች ፣ በሰንበት ትምህርት ቤቶች ፣ በየማኅበራቱ ስለ ቀናችው ሃይማኖት እና ስለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ዶግማ ቀኖናና ትውፊት መጠበቅ ጸንተው ለሚታገሉ ፤ ስለ መከረኛዋ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ቅንዓት እየተቃጠሉ መታመምን ፣ መጎሳቆልንና መነቀፍን ለሚታገሡ ፣ ‹አይ ቤተ ክርስቲያን!› ሲሉ ለሚውሉ ፤ የሰው ተመልካች ሳይፈልጉ ፣ የነገይቱን ቤተ ክርስቲያን እያሰቡ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በመድከም ዕድሜያቸውን ለሠዉ ሰው ለማያውቃቸው በልበ ሥላሴ ለተጻፉ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ይሁንልኝ!

**‹‹ያደረጋችሁትን ሥራ ስለስሙም ያሳያችሁትን ፍቅር ይረሳ ዘንድ እግዚአብሔር ዓመፀኛ አይደለም፡፡›› ዕብ.** 6.10

## መቅድም

‹‹… በዚያን ጊዜ የነበረው አገልግሎት ብዛት ያላቸው ችግሮች ነበሩበት፡፡ ሰባኪያንና የተማሩ ካህናት አልነበሩም፡፡ በመሆኑም በቤተ ክርስቲያን ድካም ሌሎች የሃይማኖት ድርጅቶች ያድጉ ጀመር፡፡ በዚህ ጊዜ መለያየትና ውስጣዊ ጠብ ተስፋፉ፡፡

ጥቂት ሰዎች ስድብን ፣ ነቀፌታንና ማንኳሰልን በይፋ ሲጠቀሙ ሌሎች ደግሞ በፍርድ ቤት ለሕግ ጉዳዮች ከፍተኛ ገንዘብ በማባከን ቤተ ክርስቲያንን ይዋጓት ጀመር፡፡ ሌሎች ግን ስለነበረው ጉዳት ያለማቋረጥ ያነቡ ነበር፡፡

ይሁን እንጂ እነዚህ ሁሉ ነገሮች ምንም ዓይነት ጥቅም አልነበራቸውም፡፡ ቤተ ክርስቲያን ከስድብ ፣ከትችት ፣ ከማንኳሰል ፣ ከመከፋፈል ፣ከፍርድ ቤት ወይም ከለቅሶ የተጠቀመችው ነገር አልነበራትም፡፡ ታዲያ ለውጥ እንዴት ሊመጣ ቻለ?

ለውጥ የመጣው እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር ሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን የአገልግሎት መሪ በነበረው በ[1]ሀቢብ ጊዮርጊስ መልካም ሥራ አማካኝነት ነው፡፡

እርሱ በዘመኑ በነበሩት ስኅተቶች ውስጥ ራሱን ሳያስገባ ሥራ ጀመረ፡፡ በወቅቱ ሁለት ወሳኝ የመሠረት ድንጋዮችን በዚያ ጣለ ፤ ለሰ/ት/ቤትና ለመንፈሳዊ ኮሌጅ፡፡ እነዚህን ነገሮች መመሥረት እንደጀመረ መሠረቶቹ በየዕለቱ ያድጉ ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ በየአብያተ ክርስቲያናቱ ፣ በየማኅበረሰቡ ፣ በየሰንበት

[1] ሀቢብ የሚለውን ስም የእኛ ሊቃውንት በመጻሕፍት ላይ ‹አቢብ› ብለው ይጠሩታል፡፡

ትምህርት ቤቱና በየመንደሩ መስበክ የጀመሩ ብዙ ቁጥር ያላቸው አገልጋዮች ታዩ። ሀቢብ ጊዮርጊስም ይህን እየተመለከተ ፡-
‹‹ሕዝብህ ፈቃድህን በመፈጸም በበረከትህ እልፍ አእላፋት ይሁኑ!›› እያለ ይዘምር ነበር።

እርሱ በጉድለቶች ላይ ነቀፌታ አልሰነዘረም ቤተ ክርስቲያን የሚጎድሏትን ነገሮች ለማቅረብ ሥራ ሠራ እንጂ።

ቤተ ክርስቲያን ሰባኪያን ይጎድሏት ነበር ፣ አብዛኞቹ ካህናት አባቶች የቅዳሴና የሥርዓት መጻሕፍትን ብቻ የሚያነብቡ ስለነበሩ የመስበክ ችሎታ አልነበራቸውም። ሀቢብ ጊዮርጊስ ግን ይህን ዓለም በቤተ ክርስቲያን ዕንባ አልሞላውም ፤ ይልቁንስ ሰባኪያንና አገልጋዮችን ማደራጀት ጀመረ እንጂ። የመንፈሳዊ ኮሌጅ ተማሪዎች የሰባኪያን ማኅበር እንዲያቋሙ አድርጓቸዋል ፤ እነዚህ ተማሪዎች ደግሞ በካይሮ ፣ በጊዛ እና በሌሎች ከከተማው ወጣ ባሉ ቦታዎች ላይ ሰማንያ አራት ቅርንጫፎችን ሊያቋቁሙ ችለዋል።

ሀቢብ ጊዮርጊስ ሕጻናትና ወጣቶች አንድ እንኳን የሚያስተምራቸው ሰው ማጣታቸውን ሲመለከትም ከዚያ ተነሥቶ ቤተ ክርስቲያንን ለመተቸት ወይም ለመውቀስ አልወደደም፤ ዛሬ በሁሉም ሥፍራ ለመስፋፋት የቻሉትን ሰንበት ትምህርት ቤቶች አቋቋመ እንጂ። ከዚህ ሌላ ለትምህርት ቤቶችንና ለቤተ ክርስቲያን ትምህርት ቤቶች መጻሕፍትን አዘጋጅቷል።

በአንዳንድ ጉባኤዎች የፕሮቴስታንቶች መዝሙር ቦታ እየያዘ ሲመጣ በቤተ ክርስቲያን ዜማ የተቃኙ መዝሙራትን ያዘጋጅ ጀመር፡፡ የእርሱ አገልግሎት በሁሉም መስክ የተስፋፋ ነበር፡፡ በሀቢብ ጊዮርጊስ የተመራው ይህ የማነቃቃት ሥራ ታላቅ ትምህርትን ሰጥቶን አልፏል፡፡››

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ
የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ
‹መንፈሳዊ አገልግሎት› ከሚል መጽሐፋቸው የተወሰደ
(አያሌው ዘኢየሱስ እንደተረጎመው)

# መግቢያ

አንዳንዶች በቅዱስ ማርቆስ ወንጌላዊ የተመሠረተችው የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ከብዙ የጨለማ ክፍላተ ዘመናት በኋላ ዘመናዊውን ኅዳሴዋን የጀመረችው ከዐሥራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ በኋላ ነው ሲሉ ይሞግታሉ፡፡ ቤተ ክርስቲያንዋ በላይዋ ተጭኖ የነበረው ጨለማ የመጣው በሁለት ታሪካዊ ክስተቶች የተነሣ ነበር፡፡ የመጀመሪያው ቤተ ክርስቲያንዋን ከሌሎች ክርስቲያኖች የለያት የኬልቄዶን ጉባኤ አሳዛኝ ውሳኔ ነበር፡፡ (451 ዓ.ም.) ሁለተኛው ደግሞ የቤተ ክርስቲያኒቱን ዋነኛ ቀደምት ይዞታዎች ያሳጣና ህልውናዋን የሸረሸረው የዐረቦች ግብፅን መውረር ነው፡፡ በእርግጥም የግብፃዊያን ምእመናን እስከ ዛሬ ድረስ መኖር ተአምርና ለዐሥራ ሦስት ክፍለ ዘመናት ያልተናወጸ እምነት ማሳያ ነው፡፡

የቤተ ክርስቲያኒቱ ኅዳሴ (ዳግም ማንሰራራት) ደግሞ ከሦስት ወሳኝ ነገሮች የተገኘ ነው ፡-

- የግብፅ የነገረ መለኮት ኮሌጅ መመሥረት
- የግብፅ ሰንበት ትምህርት ቤቶች እንቅስቃሴ
- የግብፅ በጎ አድራጊ ምእመናን መገኘት ናቸው፡፡

- ላለፉት አንድ መቶ ዓመታት የኮሌጅ ምሩቃን የኦርቶዶክሳዊውን ክርስትና ትምህርት በማስፋፋት ከፍተኛ ድርሻ ነበራቸው፡፡
- በምእመናንና ምእመናት እጅ የተዘርቶ የበቀለውና ውኃ የጠጣው ትንሽ ዘር ሰንበት ትምህርት ቤት በአምላክ ፈቃድ ፍሬን የሚሠጥ ትልቅ ዛፍ እስኪሆን ድረስና ለቁጥር ለሚያታክቱ ብዙ ሰዎች መጠለያ እስከሚሆን ድረስ አደገ፡፡
- ግብፃውያን ክርስቲያን በጎ አድራጊዎች በርካታ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን በማነጽ ፣ የቤተ ክርስቲያቱን ትምህርት ቤቶች ፣ ሆስፒታሎች ፣ ሕጻናት ማሳደጊያዎች ፣ ማተሚያ ቤቶችን በማስገንባት ትምህርትንና የእርዳታ አገልግሎቶችን ያለ መድልዎ ለግብፃውያን ሁሉ በማዳረስ ከፍተኛ ድርሻ ነበራቸው፡፡

ከእነዚህ ሦስት ተቋማት በስተጀርባ ደግሞ ራሳቸውን ትተው በእምነትና በፍቅር የሚንቀሳቀሱ ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱን አስተዳደር በመደገፍና በማበርታት የቤተ ክርስቲያኒቱን ዕድገትና ትንሣኤ የሚናፍቁ ሰዎችን የያዘ አንድ ታላቅ ሠራዊት ነበረ፡፡

ከእነዚህ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን የለውጥ ፋና ወጊዎች መካከል ቤተ ክርስቲያናችን በየዓመቱ የምታስታውሰውና በዘመኑ ከነበሩት ሁሉ ጎልቶ የወጣ ፣ የበርካታ ግብፃውያንን ትውልዶች

ልብ የነካ የርእይ ሰው ይገኝበታል፡፡ ይህ ሰው ሊቀ ዲያቆናት ሀቢብ ጊዮርጊስ ይባላል፡፡

# የርእይ ሰው

በርካታ ሰዎች የለውጥ አባት ስለሚባሉትና ይህ ስያሜም ስለሚገባቸው ፓትርያርክ ቄርሎስ 4ኛ ጽፈዋል፡፡ እርሳቸው ቤተ ክርስቲያንን ጨለማ በከበባት ወቅት ያበሩ ፓትርያርክ ነበሩ፡፡ እጅግ ብዙዎች ደግሞ የጸሎትና የተአምራት ሰው ስለነበሩት ፓትርያርክ ቄርሎስ 6ኛ ጽፈዋል፡፡ እርሳቸው ደግሞ ብዙዎቻችን ያየናቸውና በእጆቻቸው የተዳሰስን ፓትርያርክ ሲሆኑ ትጉሐን ደቀ መዛሙርቶቻቸው ደግሞ በመቶዎች የሚቆጠሩ በጸሎታቸውና በቅድስናቸው የተፈጸሙ ተአምራቶቻቸውን መዝግበው አስቀርተውልናል፡፡

በእነዚህ ሁለት አባቶች መካከል ደግሞ የግብፅ የታሪክ ሰዎች የዘነጉአቸው አንድ ሌላ ቄርሎስ አሉ፡፡ እርሳቸውም በመንበረ ማርቆስ )02ኛ ፓትርያርክ የሆኑት ቅዱስነታቸው ቄርሎስ 5ኛ ናቸው፡፡ እኚህ አባት በቤተ ክርስቲያኒቱ ታሪክ ለረዥም ጊዜ ያገለገሉ ፓትርያርክ ነበሩ፡፡ በመንበረ ማርቆስ ላይም ከሃምሳ ሁለት ዓመታት በላይ ተቀምጠው በፓትርያርክነት መርተዋል፡፡ ታዋቂው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ ኢሪስ ሀቢብ ኤል ማስሪ ‹‹ባለ ግርማ ሞገሱ ፓትርያርክ›› ሲል ገልጾአቸዋል ፤ በእርግጥም ነበሩ፡፡

የፓትርያርክ ቄርሎስ 5ኛን በጎነት ለማየት የተሳናቸው ተቺዎቻቸው ችክ ባይና አፈግፋጊ ነበሩ ብለው ይከስሷቸው ነበር፡፡ ይሁንና መለስ ብለን ስንመለከት አርቆ አስተዋይና ቆራጥ ሰው እንደነበሩ እንረዳለን፡፡ በታላቅ ርእይና ጽኑ እምነት የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ከጨለማው ዘመናት ልትወጣ የምትችለው በትምህርት እንደሆነ አውቀው ነበር፡፡ ጨለማውን ሊያሸንፍ የሚችለው ብርሃን በዚህ መንገድ እንደሚመጣ አውቀው በማይበገር መንፈስ ይህንን ግብ ለመፈጸም ጉዞ ጀመሩ፡፡ ይህ ረዥም ሒደትም መጀመር የነበረበት ከንጹሐኑ የቤተ ክርስቲያን ሕጻናት ልጆች እንደሆነም አውቀውታል፡፡

የፓትርያርክ ቄርሎስ ረዥም ዘመነ ፓትርክና ቤተ ክርስቲያን ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ያሳረፉ የግብፅ ታሪካዊ ክስተቶችን ያሳለፈ ነበር፡፡ ከእነዚህ ክስተቶች መካከል የብሪታኒያ ግብፅን መውረር (08)'2) የግብፃዊያን ክርስቲያኖች ማኅበረሰብ ምክር ቤት ኤል ማግሊስ ኤል ሚሊ መመሥረት (08)'3) እና የብሪታኒያን ቅኝ አገዛዝ በመቃወም የተደረገው ታላቁ የ09)09 አብዮት ዋነኞቹ ናቸው፡፡ እነዚህ ክስተቶች በመላው ግብፃውያን መካከል በተለይም በተማሩት ዘንድ የተጋድሎ ስሜትን ፈጠረ ፤ ክርስቲያኖቹም ከዚህ ሁኔታ የሚለዩ አልነበሩም፡፡

ፓትርያርክ ቄርሎስ ለግብፅ ገና አዲስ በነበረው የዴሞክራሲ ጽንሰ ሃሳብ ተጽእኖ ሥር የነበሩ የተማሩ ሰዎችን

ከያዘው ከግብፅ ክርስቲያን ማኅበረሰብ ምክር ቤት ጋር የተስማሙ አልነበሩም፡፡

እርሳቸው ምክር ቤቱ ሲመሠረት ገና ከመጀመሪያው ተቃውመው ነበር፡፡ ውዝግቡ የተነሣው የቤተ ክርስቲያኒቱን አስተዳደር ማን ይቆጣጠር በሚል ነበር፡፡ ከስምንት ዓመታት መራራ ጭቅጭቅና (በጠቅላይ ሚኒስትርነት ደረጃ በነበረው የምክር ቤቱ አባልና ወሳኝ ሰው ቡትሮስ ፓሳህ ጋሃሊ ሃሳብ) ፓትርያርኩ ለጥቂት ጊዜ ከተሰደዱ በኋላ በቤተ ክህነቱና በምእመናኑ መካከል የነበሩት ልዩነቶች በሰላማዊ መግባባት ተፈትተዋል፡፡

በቤተ ክርስቲያቱ ዳግመኛ ሰላም ከሰፈነ በኋላ ፓትርያርክ ቄርሎስ የቤተ ክርስቲያንን መዋቅር ዘመናዊ በማድረግና አስቀድሞ የነበሩት ቄርሎስ አራተኛ የጣሉአቸውን መሠረቶች በመገንባት ላይ አተኮሩ፡፡ ይህንን የለውጥ ርእያቸውን ለመፈጸምም በተመረጡ የምእመናን ኅብረቶች ድጋፍ ይደረግላቸው ነበር፡፡ ያ ወቅት እንደ ዮሴፍ ማንካሪዩስ ፣ ኢቅላዲዩስ ላቢብ ፣ ራፍላ ጊዮርጊስ ፣ ጊዮርጊስ ፊሎቲዮስ አዋድ ፣ ያዕቆብ ናክሃላ ሩፋይላን የመሳሰሉ በቤተ ክርስቲያኒቱ ታሪክ ፣ በመምህራንና በለውጥ ሰዎች ላይ አሻራቸውን የተዉ ታላላቅ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን አርአያዎች የተከሰቱበት ነበር፡፡ ስለዚህ ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን ተማሪ እንደ መብራት እያበሩ በሚገባ እስከሠሩ ድረስ ፓትርያርክ ቄርሎስ ሐምሳዊን

ምእመናንን የዘነጉና ቸል ያሉ ናቸው ብሎ ሊደመድም አይችልም።

በዚያን ዘመን ከነበሩት የምእመናን መሪዎች መካከል እጅግ የታወቀው ሊቀ ዲያቆናት ጊዮርጊስ ሀቢብ ነበር። እርሱን የተለየ የሚያደርገው በዘመኑ የሠራው ሥራ ብቻ አይደለም ፤ ከበስተኋላው የተዋቸውና በ09)$1 ዓ.ም ከሞተ ጀምሮ የእርሱን መንገድ ተከትለው የእርሱን በጎ ውጤቶች በረጅም ርቀት ከግብ ያደረሱትና ባለ ብሩህ አእምሮ ደቀመዛሙርቱ ናቸው።

ለሰባ አምስት ዓመታት በሕይወት የኖረው ይህ ታላቅ ሰው መላ ሕይወቱን ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል የሰጠ ሲሆን ጊዜውንና ችሎታዎቹን ሁሉ ለአገልግሎቱ ለማዋል ብሎ ጋብቻን አልፈልግም ብሎ ነበር። ርእዩ የቤተ ክርስቲያንን የክብር ትንሣኤ ማየት ነበርና በማይናወጽ ፍቅርና ትጋትም ይህንን ለማድረግ ሠርቶአል። የአገልግሎቱ ዋነኛ መገለጫዎች ፍጹምነቱና አመዛዛኝነቱ እና ከጠንካራ ሥራ ጋር የተዋሐደ ራእዩ ነበር።

በዚህም በጌታችን የተነገረውን የታላቅነት ደረጃ አገኘ ‹‹… ይህንን የሚያደርግ የሚያስተምርም በመንግሥተ ሰማያት ታላቅ ይባላል።››

ሀቢብ ጊዮርጊስ በ08)&6 በካይሮ ተወለደ ፤ አባቱ የላዕላይ ግብፅ ከተማ የቴማ ሰው ነበር። አባቱ ሲሞት ገና የአራት ዓመት ልጅ ነበረ። እናቱ በክርስቲያናዊ መንገድ ያሳደገችው ሲሆን ከሕጻንነቱ ጀምሮ ፍቅረ ቤተ ክርስቲያን በልቡ እንዲያድግ

አድርጋ አሳድጋዋለች። ይህ ባይሆን ኖሮ ባደገ ጊዜ ለቤተ ክርስቲያን የሚቀጣጠል ፍቅር ባልኖረውና ስለ ዕድገቷም ከፍተኛ ተጋድሎን ባላደረገ ነበር።

ሀቢብ ጊዮርጊስ የተማረው በፓትርያርክ ቁርሎስ አራተኛ በተመሠረተው ታላቁ የኮፕት ትምህርት ቤት ነበር። በዚያን ጊዜ ዲቁና ተቀብሎ በዘመነ ፕትርክናቸው ሁሉ ከፓትርያርኩ ጎን ነበር። ካየሁት ጊዜ ጀምሮ አድናቆትን ያሳደረብኝና በካይሮ በሚገኘው የትምህርት ኤጲስ ቆጶስ ጽሕፈት ቤት በፍሬም አድርጌ የሰቀልሁት በዲቁና ልብሰ ተክህኖ ከፓትርያርኩ አጠገብ ሆኖ የተነሣው ፎቶ ነበር።



ሀቢብ ጊዮርጊስ ከፓትርያርክ ቁርሎስ አራተኛ ጋር

ውዃንብር ከሞላባቸው የመጀመሪያዎቹ የፓትርያርክ ቁርሎስ አምስተኛ የፕትርክና ዓመታት በኋላ ፣ በተለይም የ‹ኤል ታውፊቅ ኮፕቲክ ማኅበር› አባላት (የኮፕቲክ ማኅበረሰብ ምክር

ቤት አባላትም ናቸው) ጋር ከነበረው መራራ ውዝግብ በኋላ ፓትርያርኩ የለውጥ ሒደትን ጀመሩ፡፡ የዚህ ሒደት የማዕዘን ድንጋይ ደግሞ አዳዲስ የተማሩና ብሩሃን ካህናትን ማዘጋጀት ነበር፡፡

በጁላይ 08)(3 የመሠዊያው አገልጋዮች ለመሆን ለሚጠሩ ካህናት ሁሉ የመማር ዕድልን የሚሰጥ የነገረ መለኮት ኮሌጅን ለመመሥረት አሰቡ፡፡ እንዲህ ያለውን ተቋም መመሥረት ደግሞ የገንዘብ ድጋፍን የሚጠይቅ ነው፡፡ ለዚህ ሥራ ደግሞ በሀገሪቱ ሁሉ እየዞረ ለቤተ ክርስቲያናቸው ፍቅር ያላቸውን ሰዎች ለኮሌጁ ምሥረታ ድጋፍ እንዲሰጡ ለመጠየቅ ባለ ብሩህ አእምሮውን ደቀመዝሙራቸውን ፣ በዚያን ጊዜ የ0ሥራ ሰባት ዓመት ወጣት የነበረውን ዲያቆን ሀቢብ ጊዮርጊስን መረጡ፡፡

ወጣቱ ዲያቆን ከከተማ ከተማ ፣ በየአብያተ ክርስቲያናቱ እየዞረ ስለ ነገረ መለኮት ኮሌጁ ግንባታ እና የዚህ ዓይነቱ ተቋም መመሥረት ስለሚሰጠው ጠቀሜታ ለምእመናን መስበክና ማነሣሣት ጀመረ፡፡ ከዘመቻው ሲመለስ ወደ 0ሥራ አንድ ሺህ ፓውንድ የሚሆን ገንዘብ ይዞ የተመለሰ ሲሆን ከፊሉ ከጳጳሳት የተለገሰ ሲሆን ከፊሉ ደግሞ ከጉባኤ የተገኘ ነበር፡፡ በተገኘው ምላሽም ፓትርያርኩ ከሹርባ ከተማ ዳርቻ በሚገኝ ማሃማሻ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ ትልቅ ቤት ሊገዙ ቻሉ ፤ ይህም ቤት የመጀመሪያ ኮሌጅ ሆነ፡፡

ፓትርያርኩ የሱፍ ማንካርዩስ የተባለን ምሁር የመጀመሪያው የኮሌጁ ርዕሰ መምህር አድርገው ሰየሙት፡፡ ሀቢብ ጊዮርጊስ የመጀመሪያዎቹ ተመራቂዎች ለመሆን ካመለከቱ ከመጀመሪያዎቹ ዐሥራ ሁለት ተመዝጋቢዎች አንዱ ነበር፡፡
ከነበረው የተለየ ችሎታና ከነበረው የሠለጠኑ መምህራን እጥረት የተነሣ ሀቢብ በኮሌጁ በመምህርነትም እንዲያገለግል ተጠይቆ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ሀቢብ ጊዮርጊስ በተመሳሳይ ጊዜ የኮሌጁ ተማሪም መምህርም ነበር፡፡

በማርች 07 08)(8ዓ.ም. ከኮሌጁ በተመረቀ ጊዜ ሀቢብ በኮሌጁ የመጻሕፍት ሓላፊ ሆኖ ተመደበ፡፡ ፓትርያርኩ በነበረው ጸጋ በመደነቃቸውም ሰባኪ አድርገውም መረጡት፡፡ ‹‹የክርስትና ሃይማኖት›› የሚል ርዕስ የነበረው የመጀመሪያው ስብከቱንም ከታላቆቹ የግብፅ ትምህርት ቤቶች በአንዱ አዳራሽ ሰበከ፡፡ ይህንን ስብከት ከተማሩት ሰዎች መካከል የ‹ሚስር› ጋዜጣ ባለቤት ሺኑዳ ኤል ማንካባዲ ይገኝ ነበር፡፡ በወጣቱ ሀቢብ በተሰበከው ስብከት የተደነቀው ይህ ሰው አስፈቅዶ በራሱ ወጪ በብዙ ሺህ ኮፒዎች በማሳተም አሠራጭቷል፡፡

በሌላ ጊዜ ደግሞ ወጣቱ ሀቢብ ፓትርያርኩ በተገኙበት በሀሬት አል ሳካዬን በሚገኘው በሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲሰብክ ተጋበዘ፡፡ የተቀደሱት ፓትርያርክ ወጣቱ ዲያቆን ቆሞ በሚሰብክበት ወቅት ተመስጠው

ነበር ፤ ፊታቸው በደስታ በርቶ የተማሩትን ምእመናንንም ይባርኩ ነበር፡፡

በዚያን ወቅት ሀቢብ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያንን በሁለት መንገድ ማገልገል ጀመረ፡፡ አንደኛው በነገረ መለኮት ኮሌጅ በማስተማር ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በየሥፍራው እየዞረ የሚያገለግል ሰባኪ በመሆን ነበር፡፡ ሰፊ እውቀት ያለው ፣ ጠንካራ ቃላት የሚናገርና ከሁሉም በላይ ደግሞ ሰሚዎቹ ላይ ከፍተኛ ለውጥን የሚያመጣ መንፈስ ያለበት በእውነት ጸጋ ያለው ሰባኪ ነበር፡፡ ታላቅ ጸጋ የነበረው ሰባኪ ፎአድ ባስሊ (የኋላው አባ ፎአድ ባስሊ) በአንድ ወቅት ስለ ሀቢብ ሲመሰክር ‹‹ለእኔ ሀቢብ ጊዮርጊስ ከተወለደበት ቀን ጀምሮ ሲሰብክ የነበረ ይመስለኛል ፤ ምክንያቱም ትክክለኛ ሰባኪ ነው፡፡›› ብሏል፡፡ በእዚህ አጋጣሚ የምናነሣው ቁምነገር ቢኖር ሀቢብ ጊዮርጊስ ሕይወት ራሱ በዘመኑ የነበሩ ሁሉ እንደሚመሰክሩት በራሱ ስብከት መሆኑን ነው፡፡

የግብፃውያን ብሔራዊ መሪ የነበረው አህመድ ፓሻ ኤል ሜንሻዊ በእንግሊዝ ቅኝ ገዥ ባለሥልጣናት ታስሮ ከነበረበት ሲፈታ ሀቢብ የእንኳን ደስ አለህ ንግግር አድርጎለት ነበር፡፡ ፓሻ በወጣቱ ንግግርና በበጎነቱ ተማርኮ አድናቆቱን ለመግለጽ የሁለት መቶ ሃምሳ ፓውንድ ቼክ ሥጦታ ሰጥቶታል፡፡ ሀቢብ ወዲያውኑ የተሰጠውን ገንዘብ የኮሌጁን ሕንጻ ለማደስና ለማስፋፋት እንዲውል ሰጠ፡፡

በነበረው የሁልጊዜ ቀናዒነት በኮሌጁ ዙሪያ ያገኘውን ቦታና ቤት ይገዛ ነበር ፤ በኋላም የገዛቸው ቤቶችና ቦታዎች ሲቀላቀሉ አምስት ሺህ ስኩዌር ሜትር ደርሰዋል፡፡ አንድ ጊዜም ከኮሌጁ ሕንጻ አጠገብ የሚኖሩ አረጋዊን መሬት በሥጦታ ለኮሌጁ እንዲሰጡ አሳምኖአቸዋል፡፡ በላዕላይ ግብፅ ኤል ሚና ከተማም ሰፋ ያለ ቦታ ለኮሌጁ ይገዛ ነበር፡፡

ያለ ድካም ባሳየው ትጋት የተደሰቱት ፓትርያርኩ ሊቀ ዲያቆንነት መዓርግ ሰጥተውታል፡፡ ሀቢብ ሥጦታቸውን ከታላቅ ምስጋና ጋር ከተቀበለ ከጥቂት ቀናት በኋላ ቤቱን በፓትርያርኩ ስም አስደርጎታል፡፡ ቅዱስነታቸው በመንፈሳዊ ልጃቸውን ልብ ስለሞላው መንፈሳዊ ጸጋ እጅግ ተደስተው ነበር፡፡ ስለዚህ እኚህ ፓትርያርክ በየዕለቱ እየተመላለሱ መጠየቃቸውና ትምህርቱን መማራቸው ፣ ለአገልግሎት እና ለኑሮው የሚያስፈልገውንም ነገር የሚያሟሉለት መሆናቸው አይደንቅም፡፡

ሀቢብ ጊዮርጊስ ለፓትርያርኩ ክርስቲያናዊ ፍቅር ምላሽ አልነፈገም፡፡ ከኮሌጁ ጋር አያይዞ የጳጳሳት ማረፊያ ገንብቶአል፡፡ ፓትርያርኩ ይህንን ማረፊያ በጎበኙበት ወቅት ‹‹ይህ አዲሱ መንበረ ፓትርያርክ ነው ፤ ይህንን ስፍራ መኖሪያዬ አደርገዋለሁ ፤ ሊያገኘን የሚፈልግ ሰው እዚህ መጥቶ ሊያገኘኝ ይችላል፡፡›› ብለው ነበር፡፡ አክለውም ‹‹አሁን የመጣሁት ለጥቂት ጊዜ ልቆይ ነው ፤ በሚቀጥለው ጊዜ ስመጣ ግን እቆያለሁ፡፡›› በእርግጥም ዳግመኛ ተመልሰው ለአንድ ወር በማረፊያ ቤቱ ቆይተዋል፡፡

በቆይታቸው ወቅትም በተደጋጋሚ ‹‹እንዴት ያሳዝናል? ይህ ማረፊያ ቤት መሠራት ከነበረበት ጊዜ እጅግ በጣም ዘግይቶአል ፤ ይሁንና የተሠራው መሠራት በነበረበት በትክክለኛው ጊዜ ነው፡፡››

በ1918 የኮሌጁ ርዕሰ መምህር ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ ሀቢብ ጊዮርጊስ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ሆነ፡፡ ፓትርያርኩ ከሀቢብ ጊዮርጊስ የተሻለ ይህንን ሓላፊነት ሊወጣ የሚችል ሰው አላገኙም፡፡ ሀቢብ በሠላሳ ሦስት ዓመቱ በከፍተኛ ብቃት ኮሌጁን አስተዳደረ፡፡ የሚከተለው የሹመት ደብዳቤ ፓትርያርኩ ለሀቢብ ጊዮርጊስ የጻፉለት ሲሆን ለእርሱ ያላቸውን አድናቆትም የገለጡበት ነበር ፡-

‹‹የነገረ መለኮት ትምህርቶች መምህር ለሆንከው ለተከበርኸው ምስጉን ልጄ ሊቀ ዲቆናት ሀቢብ ጊዮርጊስ የእግዚአብሔር በረከት ከአንተ ጋር ይሁን!

ከቡራኬያችንና ጸሎታችን በማስከተል የግብፅ የነገረ መለኮት ኮሌጅ ዲን ወደ እግዚአብሔር በሞት በመወሰዱ ምክንያት እና በአንተ መልካምትም ላይ ባለን እርግጠኝነት ፣ ለኮሌጁ መሻሻል ባለህ ጉጉትና በምታደርገው ድካም የለሽ ጥረት ፤ እንዲሁም ለተወደደችው ቤተ ክርስቲያናችን ባለህ እምነትና ቅናት በመተማመናችንንና በተጠቀሰው ኮሌጅ በመምህርነት ያገለገልህ በመሆንህ በኮሌጁ በመምህርነት እንድትቀጥል ከመጠየቅ ጋር የኮሌጁ ርዕሰ መምህር እንድትሆን መርጠንሃል፡፡

**አምላክ እንዲባርክህና በቸርነቱ እንዲያግዝህ ፣ በጥበቃው እንዲጋርድህና ጥረቶችህን ሁሉ እንዲያሳካልህ እንለምነዋለን፡፡ ምስጋና ሁሉ ለዘለዓለም ለእርሱ የሚገባው የእግዚአብሔር ሰላም ከአንተ ጋር ይሁን!››**

ቄርሎስ 5ኛ

*በመንበረ ማርቆስ ፓትርያርክ*

04 ሴፕቴምበር 09)08

*ሀቢብ ጊዮርጊስ ኮሌጁን በኦርቶዶክሳዊት እምነት ወደሚያበራ መብራትነት ቀየረው ፤ ከማንኛውም የውጪ ተጽዕኖም የጠበቀ አደረገው፡፡*

*ለምሳሌ በ09)#6 ዓ.ም. አንዳንድ የኮፕቲክ ማኅበረሰብ ምክር ቤት አባላት ለኮሌጁ ወጣት የነገረ መለኮት ተማሪዎች በእንግሊዝ ሀገር በሚገኝ የነገረ መለኮት ኮሌጅ የትምህርት ዕድል እንዲሰጣቸው ሀሳብ አቅርበው ነበር፡፡ ሀቢብ ጊዮርጊስ ይህንን ሃሳብ ተቃውሞ ነበር ፤ የተደረገውም ሙከራ በወቅቱ የነበሩት ፓትርያርክ ዮሳብ ካልዕ በተቃወሙት ጊዜ ከሸፈ፡፡*

*በሌላ ጊዜ ደግሞ ይኸው የኮፕት ማኅበረሰብ ምክር ቤት በግሪክ ቋንቋ በቂ እውቀት ያለው ግብጻዊ ሰው የለም በሚል ምክንያት አንድ የአንግሊካን ቄስ በኮሌጁ የጥንታዊ ግሪክ ቋንቋ መምህር ሆኖ እንዲቀጠር አቅርቦ ነበር፡፡ ሀቢብ ጊዮርጊስ ከመምህራኑ ጋር ከተወያየ በኋላ በኮሌጁ ኦርቶዶክሳዊው አስተምህሮ ተጠብቆ እንዲኖር የምክር ቤቱን ሃሳብ ውድቅ የሚያደርግ የአቋም መግለጫ አሳተሙ፡፡ ከዚህ በኋላ ታዋቂው*

ግብፃዊ የሥነ ልሳን መምህር ያሳ አብዱል መሲሕ የግሪክኛን ቋንቋ እንዲያስተምር ተመረጠ፡፡

ሀቢብ ጊዮርጊስ ምእመናን ኦርቶዶክሳዊውን እምነት ይዞ የማቆየትን ጥቅምና ይህንንም እምነት ለማሳደግ ብቁ እና ብሩህ ኅሊና ያላቸውን ቀሳውስት ማግኘት ምን ያህል እንደሚጠቅም እንዲያውቁ አድርጓል፡፡

ለዩኒቨርስቲ ተማሪዎችም በመንፈሳዊ ኮሌጁ የማታ ትምህርት ቤት ለመመሥረት ከተባባሪ ወዳጆቹ ጋር በተተደጋጋሚ ይነጋገር ነበር፡፡ ይህ የማታ ትምህርት ቤት የተከፈተው በፓትርያርክ ዮሳብ ካልዕ የፓትርክና ዘመን ነበር፡፡ እኚህ አባት በታየው ዕድገት እጅግ ይደሰቱ ነበር ፧ ይህም ደስታቸው በጳጳሳቱና በማኅበረሰቡ ምክር ቤት አባላትም ላይ ይንጸባረቅ ነበር፡፡ ይህ የማታ ትምህርት መጀመርም ኮሌጁ በግብፅ የትምህርት ሚኒስቴር እንደ ከፍተኛ ትምህርት ኮሌጅ ዕውቅና እንዲያገኝ አስችሎታል፡፡ የማታ ትምህርት ቤቱ እጅግ ብዙ ባለ ብሩህ አእምሮ የሆኑ ወጣት ምሩቃን ወደ ኮሌጁ እንዲገቡ ማርኮአቸዋል፡፡ ከእነዚህም አንዱ ታዋቂው አገልጋይና የአርት ትምህርት ምሩቅ የነበረው ናዚር ጋይድ አንዱ ነበር፡፡ ናዚር ጋይድ የዛሬው ቅዱስነታቸው አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ ናቸው፡፡

ሀቢብ ጊዮርጊስ የኮሌጁን ትምህርት በመቆጣጠርና ደረጃውን በማሳደግ ከሀገር ውጪ ኮሌጆች ጋር የሚወዳደር ደረጃ ያለው አደረገው፡፡ በብዙ ብቁ መምህራን የተደራጀ ኮሌጅ

እንዲሆን ብዙ ደከመ ፤ ሥርዓተ ትምህርቱንም የተለያዩ የፍልስፍናና የሥነ ልሳን ትምህርቶችን እንዲያካትት አድርጎ አስፋፋው፡፡

የኮሌጁ ምሩቃን ፍላጎቱ ካላቸው ክህነት ሊሰጣቸው እንዲችል ለማድረግም ብዙ ሥራን ሥርቷል፡፡ ፓትርያርክ ዮሐንስ 09ኛ ይህን ሃሳብ መቀበል ብቻ ሳይሆን ቀን የኮሌጁ ምሩቃን ክህነት የሚቀበሉበትን በግንቦት 09)" ቀን ቆርጠው ለጳጳሳት ሁሉ ደብዳቤ ጻፉ፡፡ ተመሳሳይ ደብዳቤን በ09)"1 እና 09)"7 ለጳጳሳቱ ጽፈው ነበር፡፡ ከዚህ ጊዜ በኋላ ግን ቅስና ለመቀበል የነገረ መለኮት ኮሌጁ ዲፕሎማ ያላቸው ብቻ እንዲሆኑ ቅዱስ ሲኖዶሱ ወሰነ፡፡

በሀቢብ ጊዮርጊስ እይታ ኮሌጁ የራሱ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ሊኖረው ያስፈልጋል ፤ እንደዚያ ሲሆን ተማሪዎች ቅዳሴን ፣ ጸሎትንና ስብከቶችን የመስማት ዕድል ይኖራቸዋል፡፡ ለዚህ ዓላማ ቦታ የገዛ ሲሆን ቅዳሴ ቤቱም በፓትርያርኩ በአቡነ ዮሳብ በማርች09 09)"1 ዓ.ም ተከብሯል፡፡

በ09)"8 ዓ.ም. ሀቢብ ጊዮርጊስ መንፈሳዊ ኮሌጁ የመጀመሪያዎቹን ተማሪዎች የተቀበለበትን አርባኛ ዓመት መታሰቢያ በርካታ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሓላፊዎች በተገኙበት እንዲከበር አደረገ፡፡ በዚያ ወቅትም ‹‹የነገረ መለኮት ኮሌጅ ትናንትና ዛሬ›› የሚለውን ጠቃሚ ታሪካዊ መጽሐፉንም አበርክቶአል፡፡

ስብከት ከጀመረባቸው ጥቂት ዓመታት በኋላ ሀቢብ ጊዮርጊስ መሠረት መጣል ያለበት ሕጻናት ላይ መሆኑን ተረድቶ ነበር፡፡ የቤተ ክርስቲያኒቱ ቀጣይ ትውልድ ከትንሽ ዕድሜአቸው ጀምሮ ከተማሩ ኦርቶዶሳዊ ክርስቲያናዊ እሴቶች በሰብእናቸውና በሕይወታቸው ላይ ዘልቀው ይገባሉ፡፡

ከዚህ ነጥብ ጋር በተያያዘም ከታላላቅ የሀቢብ ጊዮርጊስ ጥረት ፍሬዎች አንዱን ልንመለከት እንችላለን፡፡ የእርሱ ዓላማ ባመጣቸው ለውጦች ክብር ለማግኘት ሳይሆን የመድኃኔዓለምን መስቀል ለመሸከምና በሚቻለው ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል ነበር፡፡ ሆኖም ይህ የጥረቱ ፍሬ ብቻ እንኳን በታሪክ ውስጥ ያለውን ሥፍራ ለማሳየት የሚበቃ ነው፡፡

ዘመኑ የሚጠይቀው ትልቁ የሀቢብ ጊዮርጊስ ጥረት ፍሬ የኮፕቲክ ሰንበት ትምህርት ቤት ነው፡፡ እርሱ ዘርቶ ውሃ ያጠጣው ሰንበት ትምህርት ቤት እግዚአብሔር አሳድጎት ትልቅና ፍሬን የተሞላ ዛፍ ሊሆን ችሏል፡፡

ሀቢብ ጊዮርጊስ ሰንበት ትምህርት ቤትን የመሠረተው በ09) የ!4 ዓመት ወጣት እያለ ነበር፡፡ አገልግሎቱን የጀመረው በካይሮ አብያተ ክርስቲያናትና በኮፕቲክ ትምህርት ቤቶች አዳራሾች ውስጥ ሕጻናትን በማስተማር ነበር፡፡ የሕጻናቱ ቁጥር መጨመር አበረታታው ፤ ስለዚህም ለቤተ ክርስቲያን ያለውን ፍቅርና አስተምሮህዋን ለመጠበቅ ያለውን ቅናት የሚጋሩ ሰዎችን እገዛ ፈለገ፡፡

እግዚአብሔር ሥራውን ባርኮለት ስለነበር በ09)8 ዓ.ም. ሥርዓተ ትምህርት ለመቅረጽ ፣ በአዲሱ ለምለም መስክ ላይ የተስፋፋ ሥራን ለማየትና በአገልጋዮቹ መካከል ቀጣይነት ያለው ኅብረት ለመፍጠር ማዕከላዊ ኮሚቴ አቋቋመ፡፡

ቅርንጫፎቹም ከሰሜን የሀገሪቱ ክፍል እስከ ደቡብ ዳርቻ ድረስ በብዙ ቁጥር ተስፋፉ፡፡ በ09)#1 ዓ.ም. ቁጥሩ በመጨመሩ የተነሣ በካይሮ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ሲደረግ ተሰብሳቢዎቹ አምስት መቶ አገልጋዮች ነበሩ፡፡

በአገልጋዮቹና በተባባሪዎቹ ጥረትም ሰንበት ትምህርት ቤቱ የታወቀ ሆነ፡፡ ለቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ የሆነ አካል ሆነ፡፡ በዓመታትም ውስጥ ሰንበት ትምህርት ቤት ለጌታችን ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ እና ለኦርዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያኑ አስተምህሮ በወጣቶች ልብና ኅሊና ውስጥ ሕያው ምስክር ሆነ፡፡

የመጻሕፍትና የበራሪ ጽሑፎች ሥርጭት ፣ ዐውደ ርእያት ፣ሴሚናሮች ፣ ኮንፍራንሶች ፣ ወደ አብያተ ክርስቲያናትና ወደ ገዳማት የሚደረጉ መንፈሳዊ ጉዞዎችን የመሳሰሉ እንቅስቃሴዎች የመነጨት ከሰንበት ትምህርት ቤት ነው፡፡

በእንቅስቃሴው ወቅት የነበሩት የሀቢብ ጊዮርጊስ ተባባሪዎችም የእርሱን ሓላፊነት ተረክበው ቤተ ክርስቲያንን ካለማወቅ ጨለማ አውጥቶ ወደ ቀደመ ክብሯ መልሶ

የክርስትናውን ዓለም በብርሃንዋ የምትመራ ለማድረግ ተጋድለዋል ፤ ይህ ወቅትም ወርቃማ ዘመን ነበር፡፡

ከእነዚያ አገልጋዮች መካከል (ወጣቱ ጸሐፊና ገጣሚ ናዚር ጋይድን ጨምሮ) በ09)#7 ዓ.ም. ጀምሮ ከፍተኛ ተጽዕኖ ማሳደር የቻለ ‹‹ሰንበት ትምህርት ቤት›› የሚል ስያሜ የነበረው መንፈሳዊ መጽሔት ማዘጋጀት ጀመሩ፡፡ ለታላቁ መምህራቸው ለሀቢብ ጊዮርጊስ በነበራቸው ፍቅርም የመጽሔቱ የበላይ ጠባቂ አደረጉት፡፡ በዶ/ር ሄንሪ አል ኮሆውሊ የተጻፋ የመጽሔቱ የመጀመሪያ ርዕሰ አንቀጽም ከዚህ ታላቅ ሰው ወደ ወጣቶቹ የተሸጋገረውን ፍቅርና መንፈሳዊ ቅናት የሚያሳየን ነው፡፡ እንዲህ ብሎ ይጀምራል ፡-

‹‹በበረታው ክንድ ፤ ይኸውም በሁሉን ቻዩ አምላክ ክንድ ይህንን ‹ሰንበት ትምህርት ቤት› የተሰኘ መጽሔት ጀምረናል፡፡ ይህን መጽሔት የምናሳምበት ዓላማ እየታተሙ ያሉ ኅትመቶችን ቁጥር ለመጨመር ሳይሆን ለኮፕቲክ ማኅበረሰብ ዳግም ልደት ያለንን ፍላጎት ለመግለጽ ነው፡፡ ስለ ቤተ ክርስቲያኒቱ ለውጥ መስተጋባት ከተጀመረ ከግማሽ ምዕተ ዓመታት በላይ አልፈዋል፡፡ ሆኖም አንዳንዶች ለዚህ ለውጥ አንድ እርምጃ እንኳን አልተራመዱም፡፡ አዲስ ሕይወትን ለማግኘት እንድንችል የለውጥ በሮችን ለማንኳኳት ቁርጠኝነታችንን ማጠናከር አለብን…››

በእግዚአብሔር ቸርነት ይህ መጽሔት እስከ ዛሬ ድረስ በመታተም ላይ ይገኛል፡፡

ሌሎቹ የሀቢብ ጊዮርጊስ ተባባሪ አገልጋዮች ደግሞ በሰንበት ትምህርት ቤቶች ያሉ ወጣት ሴት አገልጋዮችን እንቅስቃሴ ለማሳደግና ኦርቶዶክሳዊውን ትምህርት የተጠናከሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሴቶች ማኅበር እንዲቋቋም ሃሳብ አቀረቡ፡፡ ሁሉም ቅርንጫፍ ሰንበት ትምህርት ቤቶችም ተመሳሳይ መዋቅርና መርሐ ግብር እንዲኖራቸውም ሃሳብ ቀረበ፡፡

ማእከላዊው ኮሚቴ ባደረገው ትዝብትም በሕጻንነታቸው ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት ለመግባት ዕድል ያልገጠማቸው በርካታ ወጣት ሴቶችና ወንዶች እንዳሉ በመታወቁ ‹‹አል ጋሜአ አል ኬፐቴአ›› የሚባል መንፈሳዊ ፣ ባህላዊና ኅሊናን የሚያድሱ አገልግሎቶች የተካተቱበት መርሐ ግብር ተዘጋጀላቸው፡፡ ይህንንም አገልግሎት እግዚአብሔር ባርኮት ብዙ ቅርንጫፎች ወዳሉት ትልቅ እንቅስቃሴነት ተቀይሮአል፡፡

እነ ሀቢብ ጊዮርጊስ የነበሩበት ዘመን አውሮፓዊ ባህልን ፣ ማኅበራዊ አመለካከትንንና ሃይማኖትን በግብፃውያን ላይ ለመጫን ከሚሞክር ከፍተኛ የውጪ ኃይል ጋር ትግል የነበረበት ነው፡፡ ወደ ክፍለ ዘመኑ መጨረሻ አጋማሽ ላይ ደግሞ ከቅኝ ገዢዎች ጋር በጥምረት የሚሠሩና አንዳንድ ጊዜም ተጽዕኖ አሳዳሪነታቸውን ለማሳደግ የቅኝ ገዢዎችን አካሔድ ይጠቀሙ የነበሩ ምዕራባውያን የወንጌል ሚስዮኖች ወደ ሀገሪቱ ገብተው ነበር፡፡ ትምህርታቸውን ግብፃውያን እንዲቀበሏቸው ሲሉም አንዳንድ ሚስዮኖች ለውጪ ዜጎች ብቻ ይሰጡ የነበሩ ዕድሎችን

ለግብፃውያን ይሰጡ ነበር፡፡ የእነርሱን እምነት መከተልም ክርስቶስን መካድ ሳይሆን የአውሮፓውያንንና የአሜሪካውያንን ዓይነት የአኗኗር መንገድ ለመከተል የተገኘ የዕድል መስኮት መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ ዓላማቸውን ለማሳካት የቤተ ክርስቲያኒቱን ልጆች ለመለወጥ በኦርቶዶክሳውያኑ ቤት በመዞር ለየቤተሰቦቹ ሊያገኙአቸው ስለሚችሉአቸው ጥቅሞች በማስተማር ፣ መጽሐፍ ቅዱስን ፣ የሚስቡ ሥዕሎችንና በራሪ ጽሑፎችን በነጻ ማደል ጀመሩ፡፡ ቀጣዩ እርምጃቸው ደግሞ በየቤቱ እየዞሩ በወጣቶችና በአረጋውያን ፊት የእናት ቤተ ክርስቲያንን ስም ጥላሸት መቀባት ነበር፡፡ ይህም ብዙ ኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን ቤተሰቦችን ከቤተ ክርስቲያናቸው የለየ ነበር፡፡

ይህንን የውጪ ሀገር ‹ወንጌላውያን› እንቅስቃሴ ለመከላከል ፓትርያርክ አቡነ ቄርሎስ 5ኛ በ09)4 ዓ.ም. አድካሚ ጉዞን ጀመሩ፡፡ ልጆቻቸው ምእመናንን ለማግኘትና ለቤተ ክርስቲያን ያላቸውን ፍቅርና ከኦርቶዶክሳዊው እምነት ጋር ያለውን ቁርኝት ለማጠናከር በናይል ወንዝ ዙሪያ የሚገኙ በርካታ ቦታዎችን ጎበኙ፡፡ ፓትርያርኩ በጉዞአቸው በሦስት ሊቃነ ጳጳሳት ታጅበው ፣ ከጸሐፊያቸውና ከሁለት ምእመናን ጋር ነበሩ፡፡ ከእነዚህም አንዱ ሀቢብ ጊዮርጊስ ሲሆን በጉዞአቸውም ወቅት የፓትርያርኩ ቃል አቀባይ ሆኖ ያገለግል ነበር፡፡ የፓትርያርኩ ጉዞ በተለይም የአሜሪካ ሚስዮን መናሃርያ በነበረችው በአስዩት ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ ከአምስት ዓመታት በኋላም ፓትርያርኩ

የመጀመሪያ ጉዞአቸውን ውጤት ለመገምገም ጉዞ ሲያደርጉ ሀቢብ ጊዮርጊስ አብሮአቸው ነበር፡፡

ሀቢብ ጊዮርጊስ ሚሲዮኖቹ የግብፅን ምእመናንን የማረኩበትን ዘመናዊ አካሔድ ያወቀውም በዚህ ጉብኝት ወቅት ሳይሆን አይቀርም፡፡ ቤተ ክርስቲያን ምእመናንን ከሰዓት በኋላ መሰብሰብና ማስተማር ፣ ለሕጻናት ሰንበት ትምህርት ቤት ማቋቋም ፣ መዝሙራትንና የግል ጸሎቶችን የመሳሰሉ ‹ወንጌላውያኑ› የሚጠቀሙባቸውን አንዳንድ ስልቶችን መጠቀም እንደምትችልም አሰበ፡፡ ሀቢብ ጊዮርጊስ የግጥም ችሎታውን በሥራ ላይ በማዋል ‹‹መንፈሳዊ መዝሙራት›› የተሰኘ መጽሐፍን አሳተመ፡፡ ከመዝሙራቱ አንዳንዶቹ የኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያንን ክብር የሚያወሱ ነበሩ፡፡ ለምሳሌ የታወቀው ‹‹የእኔ ኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን ፤ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን!›› (ካኒሳቲ ኤል ኬፕቲያ ፤ ካኒሳት ኡለላህ) የሚለው መዝሙር አንዱ ሲሆን ይህ መዝሙር እስከ ዛሬ ድረስ በጣም የሚታወቅ ነው፡፡ በዚህ መንገድ በተሳካ ሁኔታ በሌላ እምነቶች ተማርከው ለነበሩት አማራጭ ለማቅረብ ቻለ፡፡

በ09)7 ዓ.ም. የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን የክርስትና ትምህርት መግቢያ በመንግሥት ትምህርት ቤቶች እንዲሰጥ ለትምህት ሚኒስቴር አቤቱታ አቀረቡ፡፡ ሚኒስትሩ መንግሥት ምህራንንን ለማዘጋጀትም ሆነ ሥርዓተ ትምህርትን ለመቅረጽ ምንም ወጪ እንደማያወጣ በመግለጽ በሃሳባቸው ተስማማ፡፡

ፓትርያርኩም ለዚህ ጠቃሚ ሓላፊነት ሀቢብ ጊዮርጊስን የመረጡ ሲሆን እርሱም ሙሉ ጥረቱን በዚህ ጉዳይ ላይ በማድረግ ‹‹ስለ እምነት አመጣጥ አጭር መግለጫ›› በሚል ርእስ ባለ ሦስት ክፍል መጽሐፍ አዘጋጀ፡፡ መጽሐፉ ለመጀመሪያ ጊዜ የታተመው በ09)9 ዓ.ም. ሲሆን ተፈላጊ በመሆኑም በ09)03 አምስተኛ ኅትሙ ታትሟል፡፡

ቀጣዩ እርምጃ ደግሞ የክርስትናን ትምህርት ከመጀመሪያ ደረጃ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ድረስ ማስፋፋት ነው፡፡ በ09)፳7 ዓ.ም. ስምንት መጻሕፍትን ጻፈ ፣ አራቱ ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲሆኑ የቀሩት አራቱ ደግሞ ለሁለተኛ ደረጃ ነበሩ፡፡ በኋላም መጻሕፍቱ እንዲታተሙ የወቅቱ ፓትርያርክ አቡነ ዮሐንስ 09ኛ ሃሳብ አቅርበው ነበር፡፡

ሀቢብ ጊዮርጊስ ጸሐፊ ፣ አስተዳዳሪና ሰባኪነቱ በእኩል ደረጃ ተሳክተውለት ነበር፡፡ በአጠቃላይ ሠላሳ መጻሕፍትን በአረቢኛ ጽፎአል፡፡ አንዳንዶቹ መጻሕፍት እከ አሁን ድረስ ለነገረ መለኮት ተማሪዎች ጠቃሚ ማጣቀሻ ሆነው እያገለገሉ ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል ‹‹ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን›› የሚለው ለብዙ ዓመታት በርእሰ ጉዳዩ ላይ ጠቃሚ ማጣቀሻ ሆኖ አገልግሎአል፡፡ ‹‹የኦርቶዶክሳዊነት ዓለት›› የተሰኘው በኦርቶዶክስ ፣ በካቶሊክና በፕሮቴስታንት እምነቶች ዙሪያ የተጻፈው የአንጻራዊ ነገረ መለኮት መጽሐፍም ሌላው ነው፡፡ ሁለቱም መጻሕፍት ወደ እንግሊዝኛ ተተርጉመዋል፡፡

ለዐሥራ ሰባት ዓመታት ኦርቶዶክሳዊውን እምነት ሲያንጸባርቅ የኖረውን ‹አል ካርማ› (ወይን) የተሰኘውን መጽሔትም ማሳተም የጀመረው ሀቢብ ጊዮርጊስ ነበር፡፡

በዚህ ክፍለ ዘመን የታየውና አንዳዶቻችንም የዓይን ምስክሮች የሆንንለት የኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን ማንሰራራት ያለ ጥርጥር በሦስት ምክንያቶች የሆነ ነው፡፡ ሁለቱን አስቀድመን ጠቅሰናቸዋል ፤ ሰንበት ትምህርት ቤቶችና የነገረ መለኮት ኮሌጁ ናቸው፡፡ ሦስተኛው የኮፕቲክ ማኅበራትን የማቋቋም እንቅስቃሴ ነው፡፡

ባለፉት አንድ መቶ ዓመታት የተለያዩ የኅበረተሰቡን ፍላጎቶች ለማሟላት የተሰለፉ በሺህዎች የሚቆጠሩ ኮፕቲክ ማኅበራት ተቋቁመዋል፡፡ አንዳንዶቹ በዋናነት መንፈሳውያት ማኅበራት ሲሆኑ አብያተ ክርስቲያናትን በመገንባትና ሰባኪያንን ለአብያተ ክርስቲያናት የማዘጋጀት ዓላን ያነገቡ ናቸው፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ልዩ ልዩ ከተሞችና አካባቢዎች የኮፕቲክ ትምህርት ቤቶችን መሥርተዋል፡፡ የወላጅ ያጡ ሕጻናት ማሳደጊያ ፣ ቤተ መጻሕፍትና የአረጋውያን መኖሪያም የገነቡ አሉ፡፡ ‹‹አል ኢማን ኮፕቲክ ማኅበር›› እና ‹‹አል ታውፊቅ ማኅበር›› ለዚህ ዋነኛ ምሳሌዎች ናቸው፡፡ ሀቢብ ጊዮርጊስ የእነዚህ ማኅበራት መሥራች አባል ነበር፡፡ ‹አል ልማን ማዕከላዊ ኮሚቴ›፣ ‹አል ማሃባ የክርስትና ትምህርት ማኅበረሰብ› የተሰኙትን ያቋቋመው እርሱ ሲሆን እንደ ‹‹የመጽሐፍ ቅዱስ ወዳጆች ማኅበረሰብ›› ፣

‹‹ሠራዊተ ቤተ ክርስቲያን›› ፣ ‹‹የድኅነት ቃል›› ፣ ‹የነገረ መለኮት ምሩቃን ማኅበረሰብ› እና ለሌሎች ብዙ ማኅበራት መቋቋም መነሻሻ ምክንያት የሆነው ሀቢብ ጊዮርጊስ ነበር።

እነዚህ ማኅበራት በአጭር ጊዜ ውስጥ ስኬታማ ሆነው ከካይሮ በቅርብም ሆነ በሩቅ በሚገኙ ሥፍራዎች አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን ለመጀመር ቻሉ።

በዕድሜ እየገፋ ሲመጣ ሀቢብ ጊዮርጊስ ጤናውም እየታወከ መጣ። ቤቱም በበርካታ መንፈሳውያን ደቀ መዛሙርቱ መሞላት ጀመረ። ለእርሱ የነበራቸውን ፍቅርም ለመግለጽ መኝታውን ከብበው አብረውት ጸሎት በማድረግ ፣ ራሱ የደረሳቸውን መዝሙራትም ይዘምሩለት ነበር።



በኦገስት !2 09)$1 ዓ.ም. የዚህ ታላቅ ሰው ነፍስ ከሥጋዋ ስትለይ ዜና ዕረፍቱ በሀገረ ግብፅ ከዳር እስከዳር ተሰማ። ሕይወቱን ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ለሠዋው ለሀቢብ

ጊዮርጊስ ያላቸውን ፍቅርና አክብሮት ለመግለጽ ካህናት ፣ ከየማኅበረሰቡ የመጡ ምእመናንና ምእመናት ፣ የሰንበት ትምህርት ቤት አገልጋዮች እና በሺህዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በሥርዓተ ቀብሩ ላይ ተገኙ።

በ09)$1 ሴፕቴምበር !7 ለክብሩ በተዘጋጀው የመታሰቢያ ሥነ ሥርዓት ላይ በርካታ ደቀ መዛሙርቱ ለዚያ ታላቅ ሰው ያላቸውን ጥልቅ የሆነ ስሜትና አክብሮት ለመግለጽ ተገኝተው ነበር።

እንደ ዶ/ር ዋሂብ አታላ (የኋላው አቡነ ጎርጎርዮስ) የተናገረ ግን ማንም አልነበረም። ፡-

*‹‹... ከየት ልጀምር? ምንስ ልበል? ሰውን በሕይወቱ እያለ ልናመሰግነው አይገባም። አሁን ግን የምንናገርበት ጊዜ ደረሰ። ዝም ለማለትም ጊዜ አለው ፤ ለመናገርም ጊዜ አለው። ... ታዲያ ምን እንበል? ... ይህ ታላቅ ሰው በመንፈስ ከመካከላችን እያለ እኔ ልሰብክ አልችልም። እርሱ ያስተማረንን ነገር እንኳን ደግሜ ለመናገር አፍራለሁ ፤ ምክንያቱም እርሱ የተናገራቸው ቃላት እኔ ስናገራቸው ኃይላቸውን ያጣሉ ፤ እርሱ ሲናገራቸው ግን ኃይል አላቸው።*

*ለጠላትም ለወዳጅም በፍቅር የተከፈተ ልብ ነበረህ! ሁሉን ነገር አንተው ጀመርኸው ፤ ሁሉንም ሰውም አገለገልህ። መምህር ! ለፍቅርና ይቅር ባይነት የነበረህ አቅም የሚያስደንቅ ነበር። በእግዚአብሔር ላይ የነበረህ የጠነከረ እምነት በመንገድህ*

*ላይ ያጋጠሙህን እጅግ ብዙ መሰናክሎች ተስፋ ሳትቆርጥ እንድታልፋቸው አደረገህ፡፡ የዓለምን ጉዳዮችና መንፈሳዊውን ነገር ለመጨበጥ የቻለ ትልቅ ኀሊና ነበረህ፡፡ የገንዘብንና የዝናን ፍቅር በማስወገድ የልብህንና የሃሳብህን ንጽሕና ለማግኘት በሕይወትህ ሁሉ ተጋድለሃል፡፡...››*

በዚሁ የመታሰቢያ ዕለት ወጣቱ ገጣሚ ናዚር ጋይድ (የኋላው ቅዱስነታቸው አቡነ ሺኖዳ ሳልሣዊ) ለውድ መምህሩ እጅግ በሚመስጥ ግጥም መወድስ አቅርቦአል፡፡ የግጥሙ ጠቅላላ መልእክት የሚከተለው ነው፡-

*‹‹ቅድስና ፣ እምነትና ፍቅር - ይህ ነው የአንተ ዓለም፡፡ የእሾኽና የስቅለት ሕይወት፡፡ ግን አንተ ማን ነህ? መልእክተኛ ትሆን? የለም ከመልእክተኛስ ይልቅ ብሩህ ነህ! አንተ ቶሎ ቶሎ የሚመታ ልብ ነህ ፣ ሀገሪቱን ሁሉ ማቀፍ የቻለ ልብ ፣ ጥልቅ የርኀራኄና የፍቅር ምንጭ የሆነ ልብ!*

*ታላቁ ጻድቅ ሆይ!*

*መታወክ የሌለበት ጥንካሬህ እንዴት ያለ ነው? ደካማነት የሌለበት የዋህነት ፣ ትልቅነት ያለበት ባሕርይ ፣ ሁልጊዜም የሚያጠቁትን ይቅር ለማለት የተዘጋጀ ልብ ምን ዓይነት ልብ ነው? ሀቢብ ሁላችን በትከሻው ላይ እንደ ሕጻን ስንድኽበት የኖርን አባታችን ነው!››*



እናም ጸሐፊው ፣ ገጣሚው ፣ ሰባኪው ፣ አስተዳዳሪው ባለ ብዙ ጸጋው ከዚህች ዓለም ተለየ!

የኮፕቲክ ማኅበረሰብ ምክር ቤት አባል ፣ የነገረ መለኮት ፕሮፌሰር ፣ የነገረ መለኮት ኮሌጅ ርእሰ መምህር ፣ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማእከላዊ ኮሚቴ ምክትል ፕሬዝዳንት ፣ የ‹አል ካርማ› መጽሔት አሳታሚ ፣ የብዙ በጎ አድራጊ ማኅበራት አባል የነበረውና በቤተ ክርስቲያን ብዙ ሓላፊነቶችን ተሸክሞ የነበረው ሰው አረፈ።

ከሰማዕቱ ቅዱስ እስጢፋኖስ በኋላ እጅግ የታወቀው የቤተ ክርስቲያን ሊቀ ዲያቆናት ፤ እስከ አሁን ድረስ መላውን የነገረ መለኮት ተማሪ ፣ የሰንበት ትምህርት ቤት አገልጋዮችን ፣ የሚመጣውን ክርስቲያን ትውልድ ሁሉ መንፈስ የሚያነሣሣ ለምእመናን አገልጋዮች ኩራት የሆነና ሆኖ የሚቀጥል ሀቢብ ጊዮርጊስ ነው።

ሀቢብ ጊዮርጊስ ዛሬ በሰማይ የድል ነሺዎች ቤተ ክርስቲያን አባል ነው። የእርሱ ትውስታ ግን ገና የሚመጣውን ትውልድ መንፈስም የሚያነሣሣ ነው። እንዲሁም ይሁን!

# እግዚአብሔርን የመምሰል ምሥጢር

(በሚል ዐቢይ ርዕስ ተሰባስበው ከታተሙት የሊቀ ዲያቆናት ሀቢብ ጊዮርጊስ አጫጭር ጽሑፎች ውስጥ የተመረጡ ጽሑፎች)

# ሕይወት የማያቋርጥ ውጊያ ነው!

የሰው ልጅ ሕይወት ፈጽሞ በማያበቃና ፈጽሞ በማይጠናቀቅ መንፈሳዊ ውጊያና ሥነ ልቡናዊ ትግል የተሞላ ነው፡፡ ሥጋ እስካልሞተና በምኞቶች የተሞላ እስከሆነ ድረስ ዲያቢሎስ በነፍስ ላይ ጦርነትን ያውጃል ‹‹ሞት ሆይ፥ መውጊያህ የት አለ? ሲኦል ሆይ፥ ድል መንሣትህ የት አለ?›› ብለን በድል አድራጊነት እስካልጮህን ድረስ ትግሉን አያቆምም ፣ አያርፍምም፡፡ (1ቆሮ. 05.$5)

በሥጋ እስከኖርን ድረስ መሣሪያዎችና የሚንቀለቀል እሳት አለ ፣ በስውነታችን ውስጥ ያለች ነፍሳችንም ከየአቅጣጫው በኃይለኛ ነፋሳት እንደምትንገላታ በማዕበል መካከል እንዳለች መርከብ ናት፡፡ እሳቱ እንደተቀጣጠለ ምድጃ ልትሉት ትችላላችሁ ፤ ስለዚህ ሰው ሆይ በዚህች ዓለም ላይ ደህንነት አይሰማህ ፣ ምክንያቱም እየሔድክ ያለኸው እንቅፋትን በተሞላ መንገድ ላይ ነው፡፡ ጠላትህ ዲያቢሎስም አንተን ለማጠቃት የሚቻለውን ሁሉ እያደረገ ነው፡፡ ከአንተ ሕይወት ላይ ያለውን ጸጋ ሊነጥቅህ ስለሚፈልግ አንተን መዋጋት አያቆምም፡፡ ያለውን ኃይልም አንተን ለመቃወም ይጠቀማል ፣ ዕረፍት አያደርግም ፣ አንተን መዋጋትም አያቆምም፡፡ ስለዚህ ንቁና ጠንቃቃ ሁን ፣

አትመነው ፣ ተንኮሎቹንና ማሰናከያዎቹን አሳንሰህ አትመልከታቸው፡፡ ሁልጊዜም እርሱን ለመዋጋትና ድል ለማድረግ ከልዑል አምላክ ድል ከማይነሣው ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ቸርነቱን ለምን፡፡

ከፈተና ነጻ እሆናለሁ ፣ ከሕመምም ነጻ እሆናለሁ ብለህ በማመን አትታለል፡፡ እንዲህ ባሰብክ ጊዜ ‹‹ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና፤›› (1ጴጥ. 5.8) በሰላና ምቾት ውስጥ እደሆንህ ማሰብ በጀመርህ ጊዜ በአደጋ ውስጥ ነህ፡፡ ምክንያቱም በሚያስፈራ ገጽታ ዲያቢሎስ ሊዋጋህ ሽምቋል፡፡

በፈተና አትፍራ ልብህም ስለ ፈተና ምክንያት አይታወክ ምክንያቱም ፈተናውን ከተወጣህ ክፉን የማሸነፍህን ማረጋገጫ ታገኛለህ፡፡ ስለዚህ ምንም እንኳን ፈተናቹንና ማሰናከያዎቹን እያፈራረቀ ሊያስቆጣህና ሊበቀልህ ቢሞክርም ድል ታደርገው ዘንድ በእምነትህ ጽኑዕ ሁን፡፡

ይህ ጠላት በእጆቹ መዳፍ ውስጥ ያሉትን በመዋጋት ጊዜውን አያባክንም፡፡ ነገር ግን ጠንክረው የሚዋጉትንና የሚያጠቁትን ይዋጋቸዋል፡፡ አንድ ጊዜ ካሸነፍኸው ድል ሁልጊዜ የአንተ ትሆናለች በየጊዜውም ትቀጠቅጠዋለህ ፣ ከዚያም ታስደነግጠዋለህ፡፡

ወደ ፈተና እንዳትገባ የምትታገል ፣ የምትዋጋና ሁልጊዜ ንቁ ሁን፡፡ የሚንበለበለውን ክፉ ነገር ሁሉ ለማባረር እንድትችል

ሁሉንም መንፈሳዊ መሣሪያዎች ሁሉ ተጠቀም፡፡እናም ‹‹በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ፡፡ የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ፡፡ መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፉት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ፡፡

ስለዚህ በክፉው ቀን ለመቃወም፥ ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሡ፡፡ እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ፥ የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፥ በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ፤ በሁሉም ላይ ጨምራችሁ የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነትን ጋሻ አንሡ፤ የመዳንንም ራስ ቁር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ፤ በዚህም አሳብ ስለ ቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በመጽናት ሁሉ ትጉ፤›› (ኤፌ. 6.0-08)

ከጠላቱ አጠገብ ያለ ወታደር ሊያንቀላፋና ሊተኛ አይችልም ፤ ይልቅስ ሁልጊዜ ለመዋጋት ንቁና ዝግጁ ይሆናል፡፡ ጥሩ መርከበኛ የአየሩን ሁኔታ በደንብ ያጠናል ፣ በማዕበልና በሞገድ መካከል እንኳን መርከቡን ከስጥመት ለማዳን መቅዘፊያውን አይለቅም፡፡

አንተም በየጊዜው ጠላትህንና የሚያመጣብህን ፈተና ለመቃወም እንዲሁ ንቁ ፣ ጠንቃቃ ፣ ትጉህና የታጠቀ መሆን አለብህ። ጠቢብና ጥንቁቅ ሁን ፣ ጠላትህንም ሳያገኝህ አግኘው። ራስህን በነገር ሁሉ ጠብቅ ፣ ሁልጊዜም እግዚአብሔርን መጠጊያ አድርግ።

# ከጠላት ፈተናዎች ተጠንቀቅ!

ዲያቢሎስ ቀስቱን ሲወረውርብንና በውጊያው ሲያውከን ይህ በእኛ ላይ ብቻ የተደረገ ቁጣና ጠላትነት አይደለም ፤ ምክንያቱም እርሱ የእግዚአብሔርም ጠላት ነውና በእኛ ላይ ሚደርሰው መከራ በእግዚአብሔር ላይ የሚደረግ ተቃውሞ ነው፡፡ ዲያቢሎስ እግዚአብሔርን ማጥቃት ባለመቻሉ ፍጥረታቱን በማታለልና ከእርሱ ጋር ወደ ዘላለማዊ ቅጣት እንዲገቡ በማድረግ ሊበቀለው ይጥራል፡፡

የተወደድኸው ሆይ! ይህንን ነገር አስተውል! ዲያቢሎስን ስትቃወመውና ስትዋጋው ክፉን ነገር ከእናንተ እያራቅህ ብቻ አይደለም ፤ ለእግዚአብሔርም ክብር እየተዋጋህ ነው፡፡

ስለዚህም የክፉውን ዲያቢሎስ ማማለያና መደለያ በመቀበል እግዚአብሔርን ከማሳዘን ይልቅ ፈተናውን በጽናት ስትታገል በውጊያው ላይ ብትሞት ይሻልሃል፡፡

ለአፍታም ቢሆን ብቻህ እየተዋጋ እንዳህ አድርገህ አታስብ፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር በጠላትህ ላይ ድል መንሣትን ይሰጥሃል፡፡ ‹‹አቤቱ አምላክ ሆይ፥ ተነሥ እጅህም ከፍ ከፍ ትበል ድሆችን አትርሳ፡፡ ኃጢአተኛ ስለ ምን እግዚአብሔርን አስቈጣው? በልቡ፡፡ አይመራመረኝም ይላልና፡፡›› (መዝ.0.02፣03) ‹‹ጥሩርና ጋሻ ያዝ፥ እኔንም ለመርዳት ተነሥ፡፡ ሰይፍህን ምዘዝ

የሚያሳድዱኝንም መንገዳቸውን ዝጋ ነፍሴን፦ መድኃኒትሽ እኔ ነኝ በላት።›› (መዝ. "5.2፣3)

‹‹አሁንም ያዕቆብ ሆይ፥ የፈጠረህ፥ እስራኤልም ሆይ፥ የሠራህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ተቤዥቼሃለሁና አትፍራ በስምህም ጠርቼሃለሁ፥ አንተ የእኔ ነህ። በውኃ ውስጥ ባለፍህ ጊዜ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፥ በወንዞችም ውስጥ ባለፍህ ጊዜ አያሰጥሙህም በእሳትም ውስጥ በሄድህ ጊዜ አትቃጠልም፥ ነበልባሉም አይፈጅህም።››(ኢሳ.#3.1፣2)

በነፍሳችን ላይ ደካማነትን እስካላየ ድረስ ሰይጣን አያጠቃንም። ጎበዝ አዳኝ ወፎችን ለማደን እንደሚያደርገው ዲያቢሎስም ወጥመዱን ለማስገባት ሁልጊዜ ከእኛ ላይ ቀዳዳን ይፈልጋል። ብዙ ጊዜም ይዋጋናል ፣ ይሸነግለናል ፣ በምኞቶቻችንም እየገባ ያገኘናል።

አዳምን በሔዋን ፣ ሶምሶንን በምወድደው ደሊላ ፣ ንጉሥ ሰሎሞንን በእንግዶች ሴቶች ፍቅር ፣ የአስቆሮቱ ይሁዳንም በገንዘብ ፍቅር እንደጣላቸው አላየህም። ስለዚህ እንደ ጎበዝ ሐኪም ሁን ፣ ጉድለትህንና ሕመምህንም አክም ፤ ኩራትህን በትሕትናና በየዋህነት ድል አድርገው ፣ የትዕቢት በሽታህንም አንተነትህን በመናቅ ፈውሰው። በተአምራትና በታላቅ ነገሮችም ከመመካት ተጠበቅ ምክንያቱም ዲያቢሎስ ራሱ በብርሃን መልአክ መመሰል ይችላል። በስብ ውስጥ መርዙን ሊከት ፣ በማጥመጃው ዘንግ ውስጥም የመደለያ ጣፋጭ ምግብን ሊያደርግና መልካምና

ጠቃሚ ነገር ይከተላል ብለህ እንድታምን ሊያታልልህ ይችላል፡፡ አንተ ግን ፈጽሞ አትታለል ፣ በከንቱም አትነዳ፡፡ ይልቅስ ከዲያቢሎስ ጥቃት ትጠበቅ ዘንድ ሁሉን ነገር አስተውልና መርምር፡፡

ይሁዳ ጌታውን አልከዳምን? ኢዮአብስ ወዳጅና የሚታመን ሰው መስሎ አሜሳይን አልገደለውምን? (2ነገሥ. !.9) በእግዚአብሔር ታመን! ከመሪ በላይ አጥብቀህ ያዘው ፤ ሁሉን ነገር ወደ እርሱ አምጣው፡፡ ድጋፍህና መጠጊያህ አድርገው ፤ እርሱ ሁለንተናህ አድርገው፡፡

# የሕይወት ፈተናና ጥቅሙ

በስደት ሀገራችን እንግዶችና መጻተኞች ስለሆንን መላው ሕይወታችን በፈተና ፣ በችግርና በሕመም የተሞላ ነው። ስለዚህ በሕመምና በስቃይ ሸለቆ ውስጥ ሆነን መከራና ችግር ቢገጥመን አያስደንቅም።

የተወደዳችሁ ሆይ! በሌላኛው እንወድቃለን እንጂ ከፈተና ነጻ አንሆንም። ለቁስላችን መድኃኒት ሲገኝም ሌላኛው መድማት ይጀምራል።

ሌላ ሞገድ ማጥቶ ሳይመታንና ሳያሰጥመን በፊት ለጥቂትም ጊዜም ቢሆን ቀና እንላለን።

እነዚህ ሁሉ መቅሠፍቶች ጀርባችንን ያጎብጡታል ፣ ራሳችንንም ያስደፉናል።

ከሰዎችስ በዙፋን ከተቀመጡ ነገሥታትስ ቢሆን ከፈተናና ከመከራ ማምለጥ የቻለ ማነው? ማናችንም! ማንም ሰው!

ምንም እንኳን ከእኛ መካከል ይህንን ፈተና ማምለጥ የቻለ ባይኖርም ፤ ቅዱሳኑ ግን ከእኛ በላይ ተሸክመውታል። ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ይህ ስለ ክርስቶስ ተሰጥቶአችኋልና፤ ስለ እርሱ መከራ ደግሞ ልትቀበሉ እንጂ በእርሱ ልታምኑ ብቻ አይደለም፤›› ብሏል። (ፊልጵ. 1.!9)

‹‹ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ

ያስፈልገናል›› (ሐዋ. 04.!2)

ዘላለማዊ ሕይወትን ለማግኘት በብዙ መከራዎች ውስጥ ማለፍ ፍቱን መድኃኒት እና ጠቃሚ መፍተሔ ነው፡፡ መከራ ጥሩ መምህር ነው፡፡ ይህም የተባለው መከራ መልካም ጠባይን ፣ ጥበብን ፣ ትሕትናን ፣ራስን መናቅን ፣ ለስላሳነትን ፣ ፍትወትና ምኞትን መቆጣጠርን ፣ አእምሮንና እና ሃሳብን ስለሚያስተካክል ፣ ቅርፅና መሠረት ያለው ሰው መሆንን ስለሚያስተምር ነው፡፡ መከራ ትዕቢተኛውን የዋህ ፣ ቁጡውን የረጋ ፣ ተጠራጣሪውን አማኝ ፣ ግልፍተኛውን ጸጥተኛ ፣ የማይታዘዘውንም ወደ እግዚአብሔር የሚመለስ ያደርገዋል፡፡

መከራና ፈተና ትዕቢትን ከእኛ ነቅሎ ያወጣልናል፡፡ ከመታበይና ከከንቱ ውዳሴም ይጠብቀናል፡፡ እግዚብሔርንና ረዳትነቱንም እንድናውቅ ያደርገናል፡፡ በምድር ላይ ሰላምና ደህንነት እንደሌለ ማወቃችንም የማይቀር ነው ፤ ያን ጊዜ ምን ያህል ደካሞች እንደሆንን እንረዳለን፡፡

መከራዎች ቅድስናን ማግኘት እንድንችል ያለማምዱናል፡፡ ስለሚያነቁንም በጥልቅ እንቅልፍ አንወሰድም፡፡

መከራ ያነጻናል ፣ ያስተካክለናል ፤ ያጠራናል ፣ ያጥበንማል፡፡ ያለ መከራ ራስን ማወቅ በጣም ከባድ ነው ፤ ስለዚህ በመከራ ካልተፈተንን በጥንካሬያችን እንታበያለን ፣ አንዳች እንደሆንን አድርገን ማሰብ እንጀምራለን፡፡ መከራ እግዚአብሔርን እንድንፈልግና ለእርሱም እንድንንበረከክ

ያደርገናል፡፡ ሐዋርያውም ‹‹ስለዚህም በመገለጥ ታላቅነት እንዳልታበይ የሥጋዬ መውጊያ፥ እርሱም የሚጎስመኝ የሰይጣን መልእክተኛ ተሰጠኝ፤ ይኸውም እንዳልታበይ ነው፡፡›› (2ቆሮ. 02.7)

‹‹እነሆ፥ እግዚአብሔር የሚገሥጸው ሰው ምስጉን ነው ስለዚህ ሁሉን የሚችለውን የአምላክን ተግሣጽ አትናቅ፡፡ እርሱ ይሰብራል ይጠግንማል ያቈስላል፥ እጆቹም ይፈውሳሉ፡፡›› (ኢዮ. 5.07፣08)

‹‹እግዚአብሔር የወደደውን ይገሥጻልና፥ አባት የሚወድደውን ልጁን እንደሚገሥጽ፡፡›› (ምሳ. 3.02)

እስራኤላዊያን በመከራና ፈተና ጊዜ እግዚአብሔርን አጥብቀው እንደሚይዙና በጸሎትና ልመና ወደ እርሱ እንደሚያንጋጥጡ ፤ ደህንነትና ስኬትን ባገኙ ጊዜ ደግሞ እንደሚረሱትና ራሳቸውን ከእርሱም እንደሚለዩ የታወቀ ነበር፡፡

ንጉሥና ነቢይ የነበረው ዳዊት በደስታና በሐሴት ጊዜ በኃጢአት ወደቀ፡፡ በመከራው ጊዜ ግን ‹‹በመከራዬ ቀን እግዚአብሔርን ፈለግሁት ›› አለ፡፡ (መዝ. &6.2) የጠፋውም ልጅ ወደ አባ የተመለሰው ከተጎሳቆለና ራን ካወቀ በኋላ ነበር፡፡ ነቢዩ ኢሳይያስ ‹‹አቤቱ፥ በመከራ ጊዜ ፈለጉህ፥ በገሰጽሃቸውም ጊዜ ልመናቸውን ወደ አንተ አፈሰሱ፡፡›› ብሏል፡፡ (ኢሳ. !6.06)

‹‹በገደላቸውም ጊዜ ወዲያው ፈለጉት ተመለሱ ወደ እግዚአብሔርምገሠገሡ››(መዝ.&7."4)

እስካልተገረዘ ድረስ የወይን አትክልት አረንጓዴ ቅጠልን ሊያሳይና ፍሬን ሊሰጥ አይችልም፡፡ በሚገባ እስካልተወጠረና በጣት እስካተገረፈ ድረስም የበገና አውታር መልካም ድምጽን ሊሰጥ አይችልም፡፡ ጣፋጭ መዓዛ ያለው ዕጣን እስካተቃጠለ ድረስ ሊያውድ አይችልም፡፡ እውነተኛ ወርቅና ዕንቁም መሰባበርና ቅርጽ መያዝ ያስፈልገዋል፡፡ ዘርም ትልቅ ዛፍ ከመሆኑ በፊት መፈረካከስ አለበት፡፡

በዚህ መንገድ የሔዱ ቅዱሳንና ጻድቃን ሁሉ ሕይወት ይኸው ነው፡፡ ገነትን የወረሱና የሰማዩን ክብር ያገኙ ሁሉ የጠከተሉት መንገድ ይህ ነበር፡፡

ጌታህ መድኃኔዓለም በእንዲህ ዓይነቱ መንገድ ተፈትኖአል፡፡ ‹‹የተናቀ ከሰውም የተጠላ፥ የሕማም ሰው ደዌንም የሚያውቅ ነው›› ተብሎለታል፡፡ (ኢሳ. $3.3) ስለዚህ ወደ አንተ በመጣ ጊዜ መከራን አትግፋው፡፡  መከራ ባስጨነቀህ ጊዜ ዕረፍትን አትሻ ፧ ይልቅስ ጉዳይህን ወደ እግዚአብሔር አቅርብ ፣ የእርሱ ፈቃድ ይሆንህ ዘንድ ፧ በመልካምነቱ እንዲያቀርብህ ፈተናና መከራን መቋቋም ትችል ዘንድ እንዲያስታጥቅህ ለምነው ፧ መከራህንም ለሕይወትህ እንደ ታላቅ ደስታ ቁጠረው፡፡

እንደዚያ ካደረግህ መከራና ሥቃይ ለአንተ ቀላልና ጣፋጭ ልሆንልሃል፡፡ ‹‹ወንድሞቼ ሆይ፥ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ፥ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቍጠሩት ፧ ትዕግሥትም ምንም

የሚጎድላችሁ ሳይኖር ፍጹማንና ምሉዓን ትሆኑ ዘንድ ሥራውን ይፈጽም፡፡››(ያዕ.1.2-3)

‹‹ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን የአሁኑ ዘመን ሥቃይ ምንም እንዳይደለ አስባለሁ፡፡›› (ሮሜ. 8.08)

# ጌታችን ስለኛ ሲል እንዳደረገው በመከራ መጽናት

በመቅሠፍት ስትመታ ፣ በፈተናም ስትወድቅ በሙሉ ልብና በትዕግሥት ተቋቋመው እንጂ አትሸነፍ ፣ ልብህም አይታወክ፡፡ ድል እንዲነሣህ አትፍቀድለህ ይልቅስ ታገልና ድል አድርገው፡፡ መድኃኔዓለም እንደተፈተነና በብዙ መከራ ውስጥ እንዳለፈ አስታውስ ፤ ‹‹እርሱ ራሱ ተፈትኖ መከራን ስለ ተቀበለ የሚፈተኑትን ሊረዳቸው ይችላልና፡፡›› (ዕብ. 2.08) ‹‹ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ፥ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም፡፡›› (ዕብ. 4.05)

ከእርሱ ጋር መከራን ካልተቀበልን እንዴት ከእርሱ ጋር በክብር ከፍ ከፍ ልንል እንችላለን? ከእርሱ ጋር ለመኖር የምትሻ ከሆንህ በመስቀል ላይ ከተሰቃየው ከእርሱ ጋር መሞት አለብህ ፤ ስለዚህም መከራዎችህንና ፈተናዎችህን አግዝፈህ አትመልከታቸው ፣ ስለ ራስህም አትዘን፡፡

የቃየንን ክፋት እስካልተጋፈጥህ ድረስ እንደ አቤል ልትሆን አትችልም፡፡ አስቀድመህ በምድረ በዳው እስካላለፍህ ድረስ ወደ ምድረ ከነዓን ልትገባ አትችልም፡፡ ከእርሱ ጋር ስቃይን እስካልተቀበለ ድረስ ማንም ከጌታው ጋር ወደ ክብር ሊገባ አይችልም፡፡ ከእርሱ ጋር ለመኖር ከፈለግህ በሁሉ ነገር እርሱን መምሰል አለብህ፡፡ እንደሞተ ከእርሱ ጋር ልትሞት ይገባሃል ፤ እንደተሰቃየ ከእርሱ ጋር ልትሰቃይ ይገባሃል፡፡ እንደተነሣ

ያስነሣሃል ፤ ከዚያም ከእርሱ ጋር ወደ ክብር ትገባለህ። ‹‹አብረንም ደግሞ እንድንከበር አብረን መከራ ብንቀበል ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን።›› (ሮሜ. 8.07)

ፈተናዎች እያየሉ የሚያንገላቱህ ከሆነ አትረበሽ ‹‹ጌታ እግዚአብሔርን የሚያመልኩትን ከፈተና እንዴት እንዲያድን›› እወቅ። (2ጴጥ. 2.9)

ሸክላ ሠሪ ሸክላውን ሙሉ በሙሉ እስኪነድድ ድረስ እሳት ውስጥ አይተወውም። ጌጥ የሚሠራም ሰው ወርቁንና ብሩን ከሚያስፈልገው በላይ እሳት ውስጥ እንዲቆይ አያደርገውም። እግዚአብሔርም አንተን በፈተና ነበልባል ውስጥ አይተውህም። ‹‹ለሰው ሁሉ ከሚሆነው በቀር ምንም ፈተና አልደረሰባችሁም፤ ነገር ግን ከሚቻላችሁ መጠን ይልቅ ትፈተኑ ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ ነው፥ ትታገሡም ዘንድ እንድትችሉ ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል።››(1ቆሮ. 0.03)

ፈተናዎችን ፣ችግሮችን ፣ ሕመምን ፣ መታወክን ፣ ጥቃትን ፣ መሰደብን ፣ መታማትን ፣ የሌሎች በአንተ ማፌዝን በደስታና በጽናት ተቀበል። ቅዱስ ያዕቆብ እንዳለው ‹‹ወንድሞቼ ሆይ፥ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ፥ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቍጠሩት›› (ያዕ. 1.2) ክርስቶስን በፊትህ ምሳሌ አድርገህ ስታስቀምጥ ችግሮች ሁሉ ቀላል ይሆናሉ። እርሱ በነገር ሁሉ

ተፈትኖአል ፣ ተሰቃይቶአል ስለዚህ የሚፈተኑትን ሁሉ ሊረዳቸው ይቻለዋል። በድህነት ብትሰቃይ ፣ በብርድ ብትንገላታ ፣ ልብስና መጠለያም ብታጣ ‹‹ለቀበሮዎች ጉድጓድ ለሰማይም ወፎች መሳፈሪያ አላቸው፥ ለሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያስጠጋበት የለውም አለው።›› የሚለውን ቃል አስብ። (ማቴ. 8.!)

‹‹የሕማም ሰው ደዌንም የሚያውቅ ነው ፤ በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸክሞአል›› (ኢሳ. $3.3፣4)

እውነተኛ ታማኝ ወዳጅህን ስታጣ ጌታችን ስለ ወዳጁ ስለ አልዓዛር እንዳለቀሰ አስታውስ። ከወዳጆችህ አንዱ ቢከዳህ ጌታንም ከወዳጆቹና ደቀ መዛሙርቱ መካከል የነበረ አብሮት የበላ ወዳጁ ለጠላቶቹ በሠላሳ ብር እንደሸጠው አስታውስ።

በሐሰት ብትከሰስ ወይም ሌሎች ቢጠራጠሩህ ፣ ቢዋሹብህና ቢያሙህ አትናወጽ ። ይልቅስ ሐሜት ፣ ክፉ ስም ፣ ስድብና ውሸት እንደተሳለ ሰይፍ በጌታችን ልብ ውስጥ እንዳለፉ አስታውስ። ‹‹ሰካራም .. የኃጢአተኞችና የቀራጮች ወዳጅ!›› ብለውታል፡ ከንፈራቸውን በላዩ ምላሳቸውንም በእርሱ ላይ ለመናገር አውጥተዋል። አንተም እንዲህ ያለው ነገር ሲገጥምህ ከአንተ በፊት ጌታ ይህ እንደደረሰበትና እርሱ ሊረዳህ እንደሚቻለው አስብ።

‹‹እርሱ ራሱ ተፈትኖ መከራን ስለ ተቀበለ የሚፈተኑትን ሊረዳቸው ይችላልና።›› በእርጋታህና በሰላምህ ጸንተህ ቆይ። የእምነትህ ጥንካሬና ትዕግሥትህ ድል እንዲነሣ አድርግ እንጂ

ፈተናዎች እንዲጥሉህ አትፍቀድላቸው፡፡

ከዋክብት ሊያበሩ የሚችሉት በጨለማ ውስጥ ብቻ ነው፡፡ ጀግና ወታደርም ጥንካሬውን ሊያሳይ የሚችለው በጦርነት ወቅት ብቻ ነው፡፡ ጥሩ መርከበኛም ወጀብና ማዕበል ካልተነሣ በቀር ችሎታውን ሊያሳይ አይችልም፡፡ ስለዚህ ፈተና ሲመጣና የኀዘንን ሸክም በላይህ ላይ ሲጭንብህ በጸጋ ለማደግህና ትዕግሥትህን ለመጨመር ፣ ጌታችንን ለመከተል ምክንያት እንደሆነ ተረዳ፡፡ እስራኤላውያን በጸጋና በቁጥር ያደጉት በመከራቸው ጊዜ ነው፡፡

ውኃ ወደ ላይ ከፍ ባለ ቁጥር መርከቡም ከፍ ይላል ፤ ፈተናህና መከራህም በቅድስና ወደ ላይ ከፍ የሚያደርጉህ ናቸው፡፡

እነዚህ ሁሉ የደህንነት ወደብ ፣ የሚታመኑበት ጋሻ ፣ የማይሰበር ምሽግ ወደሆነው ወደ ጌታችን ወደ መድኃኒታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ፈጥነህ እንድትደርስ ያደርጉሃል፡፡

# ሳይቀጣጠሉ በፊት ጥቃቅን ነገሮችን እወቃቸው!

በመጀመሪያ ትንሽና ዋጋ ቢስ መስለው የሚታዩ ነገሮችን ከተቻለህ ከመጀመሪያው እወቃቸው፡፡ ሊታላላቅ ኃጢአቶች ከምትጠነቀቀው በላይ ንቁ ሁንባቸው፡፡ ምክንያቱም ትትልልቆቹ የሚመጡት ከትንንሾቹ ነው ፤ ሰደድ እሳትም የሚጀምረው ከትንሽ ብልጭታ ነው፡፡ ሰውም በተፈጥሮም ሆነ በመንፈሳዊነት ወደ ፍጹምነት የሚደርሰው ቀስ በቀስ ነው፡፡

ሕጻን ልጅ አድጎ ወደ ወጣትነትና ወደ ሽምግልና ይደረሳል፡፡ ተክልም ቀስ ብሎ ያድጋል፡፡ ቤትም በአንድ ጊዜ አይፈርስም፡፡ በመጀመሪያ መሠረቱ ይዳከማል፡፡ ከዚያም ምሰሶዎቹ ይዳከሙና ይፈራርሳል፡፡ ኀሊናም እንዲሁ ነው ፣ በትንሽ ነገሮች ይታወክና ቀስ በቀስ ታላላቅ ኃጢአቶች ይለምዳል ፣ ያለ ፍርሃትም መፈጸም ይጀምራል፡፡

በአሸዋ ላይ ከገነባህ ነፋስ የቤትህን መሠረት ያነዋውጽብሃል፡፡ ውሽንፍርም በቀላሉ ይገባና ቤትህን ያፈራርሰዋል፡፡

እነዚህ ስትጀምራቸው ያላሳሰቡህ ትንንሽ መነዋወጾችና ትንንሽ ልማዶች ለመላቀቅና ለመተው አስቸጋሪ ወደሆኑ የኃጢአት መንገዶች ይመሩሃል፡፡

ቶሎ አይተህ ካገደልከውና ካላጠፋኸው የናቅኸው ትንሽ

ትል ወደ አደገኛና መርዘኛ ዕባብነት ሊቀየርና ለሕይወትህ ስጋት ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ በቁጥጥሩ ሥር የሚያደርግህ አደገኛ አውሬ ከመሆኑ በፊት በአንተ ቁጥጥር እስከምታደርገው ድረስ ተዋጋው፡፡

የተዳፈነና አመድ የመሰለ እሳትን በሚገባ እስካጠፋኸው ድረስ ሊስፋፋና ትልቅ ጥፋት ወደሚያደርስ ቃጠሎነት ሊቀየር ይችላል፡፡

ትንሹ ደቦል በጥቂት ጊዜ ውስጥ አድጎ ትልቅ አንበሳ ይሆናል ፤ ሳይቦጫጭቅህ በፊት አሁኑኑ ግደለው፡፡

‹‹የወይናችንን ቦታ የሚያጠፉትን ቀበሮች፥ ጥቃቅኑን ቀበሮች አጥምዳችሁ ያዙልን፡፡›› (መኃ. 2.05) እንደ ቁጣ ፣ ጥቃቅን ኃጢአት ፣ ንጹሕ ያልሆነ እይታ ፣ ነዚህ ጥቃቅን ነገሮች ‹እንዲያው ለማየት ብቻ› በሚል ሲሆን በኋላ ግን ወደ መዝናኛነት ይቀየራሉ ፣ ወደ ልማድነትም ያድጋሉ ፤ወደ ርኩሰትና መቆሸሽም ይሰፋሉ ፤ የኅሊናን ንጽሕና የሚያሳጡ እነዚህ ክፉ ምስሎች በልብና በሃሳብ ታትመው ይቀራሉ፡፡ ስለዚህ ንቃ ፤ ከመሬት ለመንቀል ወደሚያስቸግር ትልቅ ዛፍነት ከማደጉ በፊት ገና ሣር እያለ ንቀለው፡፡

ትንሽ ነው ብለህ ስለየትኛውም ኃጢአት ግዴለሽና ቀስስተኛ አትሁን ፤ በኋላ እንደባሪያ የሚያስርህና የሚያንገላታህ ቁጡና ጨካኝ ጌታህ ሆኖ ታገኘዋለህ፡፡

አንድ ሰው ስለ ትልልቅ ኃጢአቶችና እንዴት ከእነርሱ

ለማምለጥ እንደሚችል ፣ እንዴትስ ሊላቀቃቸውና ነቅሎ ሊያወጣቸው እንደሚችል ያስባል፡፡ ስለ ጥቃቅኖቹ ኃጢአቶች ግን ምንም ቦታ አይሰጥም ፤ እነርሱንም ለማጥፋት አይጨነቅም፡፡ ለዚህም ነው በቀላሉ ሲወድቅና ቀስ በቀስ እየታሰረ ፣ ትንንሾቹ ሰንሰለቶች ለመፍታት ወደሚያዳግቱ ወደ ከባድ የብረት ሰንሰለቶች ሲለወጡ የምናየው፡፡

መርከብ በታላቅ ወጀብና ሞገድ ምክንያት እንደሚሰጥመው ሁሉ በወለሉ ላይ ባለች ትንሽ ቀዳዳ ምክንያትም ሊሰጥም ይችላል፡፡ ከታላላቅ የኃጢአት ሸክም ከተላቀቅህ ትንንሽ ጥፋትን ነቅተህ ጠብቅ ፣ አሳንሰህ አትየው፡፡ መርከብህ ትልልቅ ዓለቶችንንና ከባድ ማዕበልን አልፋ መጥታ ቢሆን እንኳን ከታንሽ ነፋስና ማዕበልም ተጠንቀቅ፡፡

# በፈተናና በመከራ ጊዜ በእግዚአብሔር ታመን

ከእግዚአብሔር ጋር እስከሆንህ ድረስ ጠላትህ ከአንተ በላይ እንዳለው አድርገህ በማሰብ በፈተናና መከራ ጊዜ አትሸነፍ፡፡ የዲያቢሎስን ኃይል ያደክም ዘንድ ሥልጣኑንም ይሽር ዘንድ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ይሆናል፡፡

ጠላት እንደ ቁጡ አንበሳና እንደ ድል አድራጊ ጀግና መስሎ የሚታየው ለፈሪዎችና ለደካሞች ነው እንጂ ፤ በትግላቸው ሁሉ እግዚአብሔርን መጠጊያ ለማያደርጉ ነው እንጂ ለሚቃወሙት አይደለም፡፡

እውነታው ዲያቢሎስ የተናቀ ውሻ መሆኑ ነው፡፡ ለማይሰሙትና በእግዚአብሔር ለሚታመኑ ተስፋቸውንም በክርስቶስና በተሰጣቸው ተስፋ ላይ ለሚያደርጉ ሰዎች ሊደበቅ የሚሞክር ፈሪ ነው፡፡

እኛ ራሳችን ካልሳብነው ዲያቢሎስ በፈተናዎች ሊያጠቃን አይችልም፡፡ እርሱ ሊቀርበን የሚሞክረው እንደ መካሪ ነው ፤ እኛም እንቀበለዋለን፡፡ ተቃውመንከተዋጋነው ግን ከአጠገባችን ለመራቅ ይሮጣል፡፡ ፈታኝ ሆኖ ወደ ጌታ በቀረበ ጊዜ ራሱን እንዲወረውር ለጌታችን ነግሮት ነበር ፤ ጌታችን ግን ‹‹ጌታ አምላክህን አትፈታተነው›› በማለት ድል አድርጎታል፡፡ (ማቴ. 4.7)

የጌታን ፈለግ መከተል ድልን ያጎናጽፍሃል ፤ ዲያቢሎስም ከላይ ሊወረውርህ አይችልም፡፡ ድል እንድታደርገው ጸንተህ እየተዋጋህ ገሥጸው ፤ በሁሉ ሥፍራ ያለ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር እንዳለና እየተዋጋህ እንዳለህ እንደሚያይ እመን፡፡ ስለዚህም በጠላትህ ላይ ድል መንሣትን ይሰጥሃል ፤ መላእክቱን ልኮ ይከልልሃልና አትደናቀፍም አትወድቅምም፡፡

በዚህ ካመንህና ከተማመንህ ትበረታለህ ፤ ጸንተህም ትቆማለህ፡፡ ልብህ ከፍልሚያ ባለ ድልና ከድል አድራጊ በሚወጣ ብርታት ይሞላል፡፡ ‹‹እግዚአብሔር ልቡ በእርሱ ዘንድ ፍጹም የሆነውን ያጸና ዘንድ ዓይኖቹ በምድር ሁሉ ይመለከታሉና፡፡›› (2ዜና 06.9)

‹‹ሁልጊዜ እግዚአብሔርን በፊቴ አየዋለሁ በቀኜ ነውና አልታወክም፡፡ ስለዚህ ልቤን ደስ አለው ምላሴም ሐሴት አደረገች ሥጋዬም ደግሞ በተስፋ ታድራለች›› (መዝ. 06.8-9)

‹‹እግዚአብሔር ግን እንደ ኃያልና እንደ ጨካኝ ከእኔ ጋር ነው ስለዚህ አሳዳጆቼ ይሰናከላሉ አያሸንፉም አይከናወንላቸውምና በጽኑ እፍረት ያፍራሉ፥ ለዘላለምም በማይረሳ ጕስቍልና ይጐሰቍላሉ፡፡›› (ኤር. !.01)

ጌታችን ለቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ብሎታል ፡- ‹‹ጸጋዬ ይበቃሃል፥ ኃይሌ በድካም ይፈጸማልና አለኝ፡፡›› (2ቆሮ.02.9 ፣ 0) ‹‹ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ፡፡›› (ፊልጵ. 4.03)

እግዚአብሔርም አለ ‹‹እኔም ኤፍሬምን ክንዱን ይዤ በእግሩ እንዲሄድ መራሁት እኔም እፈውሳቸው እንደ ነበርሁ አላወቁም፡፡ በሰው ገመድ በፍቅርም እስራት ሳብኋቸው ለእነርሱም ቀምበርን ከጫንቃቸው ላይ እንደሚያነሣ ሆንሁ፥ ድርቆሽም ጣልሁላቸው፡፡›› (ሆሴ. 01.3-4)

‹‹በፊታችሁ የሚሄደው አምላካችሁ እግዚአብሔር፥ እናንተ ስታዩ በግብፅና በምድረ በዳ እንዳደረገላችሁ ሁሉ፥ ስለ እናንተ ይዋጋል ፤ ወደዚህም ስፍራ እስክትመጡ ድረስ በሄዳችሁበት መንገድ ሁሉ፥ ሰው ልጁን እንዲሸከም አምላክህ እግዚአብሔር እንደተሸከመህ አንተ አይተሃል፡፡›› (ዘዳ. 1."-"1)

‹‹በምድረ በዳ በጥማት፥ የነፋስ ጩኸትም በሞላበት ውድማ አገኘው፤ ከበበው ተጠነቀቀለትም፤ እንደ ዓይን ብሌን ጠበቀው፡፡›› (ዘዳ. "2.0)

‹‹ኃይልን የሚያስታጥቀኝ መንገዴንም የሚያቃና፥ እግሮቼን እንደ ብሖር እግሮች የሚያረታ በኮረብቶችም የሚያቆመኝ እግዚአብሔር ነው፡፡ ለሰልፍም ኃይልን ታስታጥቀኛለህ በበላዬ የቆሙትን ሁሉ በበታቼ ታስገዛቸዋለህ፡፡›› (መዝ. 08."2-"3 ፣"9)

‹‹በማዳንህ ደስ ይለናል በአምላካችን ስም ከፍ ከፍ እንላለን ልመናህን ሁሉ እግዚአብሔር ይፈጽምልህ፡፡... እነዚያ በሰረገላ እነዚያም በፈረስ ይታመናሉ እኛ ግን በአምላካችን በእግዚአብሔር

ስም ከፍ ከፍ እንላለን:: ... እነርሱ ተሰነካክለው ወደቁ እኛ ግን ተነሣን፥ ጸንተንም ቆምን::›› (መዝ. 09.5 ፣7 ፣8)

‹‹ረድኤታችን ሰማይንና ምድርን በሠራ በእግዚአብሔር ስም ነው::›› (መዝ. )!3.8)

‹‹ለደካማ ኃይልን ይሰጣል፥ ጕልበት ለሌለውም ብርታትን ይጨምራል:: ብላቴኖች ይደክማሉ ይታክቱማል፥ ጐበዛዝቱም ፈጽሞ ይወድቃሉ ፤ እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን ያድሳሉ እንደ ንስር በክንፍ ይወጣሉ ይሮጣሉ፥ አይታክቱም ይሄዳሉ፥ አይደክሙም::›› (ኢሳ. #.!9-"1)

‹‹ተቤዥቼሃለሁና አትፍራ በስምህም ጠርቼሃለሁ፥ አንተ የእኔ ነህ:: በውኃ ውስጥ ባለፍህ ጊዜ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፥ በወንዞችም ውስጥ ባለፍህ ጊዜ አያሰጥሙህም በእሳትም ውስጥ በሄድህ ጊዜ አትቃጠልም፥ ነበልባሉም አይፈጅህም:: እኔ የእስራኤል ቅዱስ አምላክህ እግዚአብሔር መድኃኒትህ ነኝ›› (ኢሳ. #3.1-3)

‹‹ጽኑ፥ አይዞአችሁ፥ አትፍሩ፥ ከፊታቸውም አትደንግጡ አምላክህ እግዚአብሔር እርሱ ከአንተ ጋር ይሄዳል አይጥልህም፥ አይተውህም::›› (ዘዳ. "1.6)

‹‹በፊትህ እሄዳለሁ ተራሮችንም ትክክል አደርጋለሁ፥ የናሱንም ደጆች እሰብራለሁ የብረቱንም መወርወሪያዎች እቈርጣለሁ›› (ኢሳ. #5.2)

‹‹እኔ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ እኔ አምላክህ ነኝና አትደንግጥ አበረታሃለሁ፥ እረዳህማለሁ፥ በጽድቄም ቀኝ ደግፌ እይዝሃለሁ። እነሆ የሚቆጡህ ሁሉ ያፍራሉ፥ ይዋረዱማል የሚከራከሩህም እንዳልነበሩ ይሆናሉ፥ ይጠፉማል። የሚያጣሉህንም ትሻቸዋለህ አታገኛቸውምም፥ የሚዋጉህም እንዳልነበሩና እንደ ምናምን ይሆናሉ። እኔ አምላክህ እግዚአብሔር፦ አትፍራ፥ እረዳሃለሁ ብዬ ቀኝህን እይዛለሁና።›› (ዘዳ. #1.0-03)

አትታወክ ፤ በእግዚአብሔርም ሁልጊዜ ታመን ፤ አምላክ ከአንተ ጋር ነውና አይተውህምና!

# በእግዚአብሔር ታመን እርሱንም መጠጊያ አድርግ

‹‹በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፥ በራስህም ማስተዋል አትደገፍ›› (ምሳ. 3.5) ‹‹በእግዚአብሔር የታመኑ እንደማይታወክ ለዘላለም እንደሚኖር እንደ ጽዮን ተራራ ናቸው፡፡›› (መዝ. )!4.1) ‹‹ትካዜህን በእግዚአብሔር ላይ ጣል፥ እርሱም ይደግፍሃል ለጻድቁም ለዘላለም ሁከትን አይሰጠውም፡፡›› (መዝ. $4.!2) ሁልጊዜ በእግዚአብሔር ተደገፍ እርሱ በመከራ ጊዜ አይተውህም እንድትናወጽም አይፈቅድም፡፡

ከጭቃ የሠራህ ፈጣሪ ፣ ከመፍጠሩም በፊት ስለ አንተ ሁሉን የሚያውቅ ፈጣሪህ ፈጥሮ ይተወኛል ብለህ ፈጽሞ አታስብ፡፡

በእግዚአብሔር ከተደገፍህ በምድር ላይ ምንም ነገር አያውክህም ፤ የትኛውም ጠላት አያሸንፍህም፡፡

አንድ ሰው በመሬት ላይ ድንጋይ ቢወረውር ወይም በኮረብታ ላይ ቀስቱን ቢወረውር መሬቱም አይፈርስም ኮረብታውም አይናወጽም፡፡ እንደዚሁ የእግዚአብሔርን ኃይልና ጥሩር ከለበስህ ፣ በብርታቱም ውስጥ ከተከለልህ ፣ በክንፎቹም ውስጥ ከተሸሸግህ ጠላት ሊያሸንፍህ አይቻለውም ፣ በሁሉም አቅጣጫዎች የእግዚአብሔር ኃይል ይጋርድሃልና ተመልሰህ ማጥቃትህም የማይቀር ነው፡፡

እግዚአብሔር ከሰይጣን የሚወረወሩ የእሳት ፍላጻዎችን ይመክታል ፣ በሕዝቡ ላይ የሚነሡ ሞገዶችንም ይገሥጻል። ለሚሹት ሁሉ እርሱ መጠጊያ ነው ፣ ለሚጋደሉ ሁሉም ብርታቸው ነው ፤ ረዳት ለሌላቸው ረዳታቸው ነው ፣ ለተከፉት ደስታቸው ነው ፤ ላዘኑትም ፍስሐቸው ነው ፤ ለተናቁትም ክብራቸው ነው። ‹‹አንተ ግን አቤቱ፥ መጠጊያዬ ነህ፥ ክብሬንና ራሴንም ከፍ ከፍ የምታደርገው አንተ ነህ። በቃሌ ወደ እግዚአብሔር እጮሃለሁ ከተቀደሰ ተራራውም ይሰማኛል።›› (መዝ. 3.3-4)

ጌታ አምላክህ ረዳትህና ብርታትህ ነውና አትፍራ አትጨነቅም። በምድር ላይ በሚኖርህ ረዥም ጉዞ ፣ በአሰልቺው መንገድህ ሁሉ ከአንተ ጋር ነው። በየትኛውም ቦታ ያአንተን መድረስ ሲጠባበቅ ታገኘዋለህ። (ሉቃ. 05) በእያንዳንዱ ጸጥታ ውስጥ እንኳን እርሱ ሊረዳህ ፣ ሊያጽናናህና ሊያበረታህ ከአጠገብህ ነው።

በእያንዳንዱ እርምጃና ሒደት የመድኃኔዓለምን ዱካውን ታያለህ ምክንያቱም በመከራም ሆነ በሰላሙ ጊዜ ፣ በጥልቁም ሆነ በዳርቻው ፣ በባሕርም ውስጥ ሆነ በእሳት ውስጥ! የትኛውም ቦታ ከአንተ ጋር ነው። በዚያ ሁሉ ነገር ውስጥ መድኃኔዓለም ለአንተ ሲል ከአንተ ቀድሞ እየጠበቀህ ወይም ከፊት ፊትህ ወይም ከጎንህ ይገኛል።

ወፍ በጎጆዋ ውስጥ እንደምትሸሸግ በአምላክህ ውስጥ ተሸሸግ። ከአዳኞች ወንጭፍ ለመዳን ወፍ ወደ ላይ ከፍ ብላ ትበርራለች። አንተም ሊያጠምድህ ከሚሞክረው ከጠላት መዳፍ እንድትድን የአምላክን ምሕረት እንደ ክንፎችህ እና እንደ ጠንካራ ክንዶችህ አድርግ። ‹‹ማረኝ፥ አቤቱ፥ ማረኝ፥ ነፍሴ አንተን ታምናለችና ጉዳት እስክታልፍ ድረስ በክንፎችህ ጥላ እታመናለሁ። ወደሚረዳኝ እግዚአብሔር ወደ ልዑል እግዚአብሔር እጮኻለሁ። ከሰማይ ልኮ አዳነኝ፥ ለረገጡኝም ውርደትን ሰጣቸው እግዚአብሔር ቸርነቱንና እውነቱን ላከ።›› (መዝ. $7.1-3)

ያለ መርከብ ባሕርን ልትሻገር አትችልም ፤ ስለዚህ በመከራዎች መካከል እንድታልፍ የሚያስችልህን የመንፈስ መርከብ ያዝ። ወደ ደህንነት ወደብና ወደ ዘለዓለማዊ ዕረፍትም ድረስ።

እንደ ሕጻን ልጅ ሁን! ሕጻን ልጅ ሲያለቅስ በእናቱ እቅፍ መጠጊያን ያገኛል ፤ አንተም በችግርና በመከራህ ጊዜ በአባታዊ እቅፉ ውስጥ ተጠጋ። ኤሊ ጠላት በመጣባት ጊዜ በላይዋላይ ባለው በደበቂያ ድንጋይ ውስጥ ትደበቃለች ፤ ጃርትም ጠላት ስታይ እንደ ኳስ ትጠቀለላለች ፤ እሾኾችዋንም ለመከላከያነት ትጠቀምባቸዋለች ፤ አንተም እንዲሁ ሁን። ፈጥነህ በምሽግህ ውስጥ ከተደበቅህ ጠላት ሊዋጋህ አይችልም። እግዚአብሔርን

መጠጊያ ካደረግህ ጠላት ሊደርስብህ አይችልም። ወደ ምሽጉ ውስጥ ከገባህ አውሬው ሊቦጫጭቅህ አይችልም።

የእግዚአብሔር ከለላነት ያላቸው ሰዎች ሌላ ነገር እንዲያበረታቸውና እንዲከልላቸው አይፈልጉም። ምክንያቱም እግዚአብሔር ደህንነታቸውና ጠባቂያቸው ስለሆነ ነው። የእግዚአብሔር ጥበቃና ከለላነት ከቁልፎችና ከጋሻዎች በላይ ነው።

እጅግ ብዙና ታላላቅ የእስራኤል ጠባቂዎች በሚተኛ ሰዓት ይጠብቁት ነበር ፤ እርሱስ የሰላም እንቅልፍ ይተኛ ነበር? አባቱ ዳዊትን ደግሞ ደሙን የተጠሙ ጠላቶቹ ይከተሉት ነበር ፤ እርሱ ግን መሬትን እንደ አልጋ ሰማይን እንደ ከለላ አድርጎ ይኖር ነበር። በሚጠብቀው እግዚአብሔር እቅፍ ውስጥ ሰላምን አገኘ ፤ እግዚአብሔርን እንደ ምቹ ትራስ አድርጎ ምቹና ጣፋጭ እንቅልፍን ይተኛ ነበር። እግዚአብሔርን መጠጊያ ማድረግ ለእርሱ ምርጥ መጠለያ ፣ የሚሞቅና የሚለሰልስ ልብስ ነበር።

‹‹በተጨነቅሁ ጊዜ እግዚአብሔርን ጠራሁት ሰማኝ አሰፋልኝም ፤ እግዚአብሔር ረዳቴ ነው፥ አልፈራም ሰው ምን ያደርገኛል? እግዚአብሔር ረዳቴ ነው፥ እኔም በጠላቶቼ ላይ አያለሁ። በሰው ከመታመን ይልቅ በእግዚአብሔር መታመን ይሻላል። በገዦች ተስፋ ከማድረግ ይልቅ በእግዚአብሔር ተስፋ ማድረግ ይሻላል። አሕዛብ ሁሉ ከበቡኝ፥ በእግዚአብሔርም ስም አሸነፍኋቸው ፤ መክበቡንስ ከበቡኝ፥ በእግዚአብሔርም ስም አሸነፍኋቸው ፤ ንብ

ማርን እንዲከብብ ከበቡኝ፥ እሳትም በእሾህ ውስጥ እንዲነድድ ነደዱ፥ በእግዚአብሔርም ስም አሸነፍኋቸው። ገፉኸኝ፥ ለመውደቅም ተንገዳገድሁ እግዚአብሔር ግን አገዘኝ። ኃይሌም ዝማሬዬም እግዚአብሔር ነው፥ እርሱም መድኃኒት ሆነልኝ። የእልልታና የመድኃኒት ድምፅ በጻድቃን ድንኳን ነው የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች። የእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ አደረገችኝ የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች። አልሞትም በሕይወት እኖራለሁ እንጂ፥ የእግዚአብሔርንም ሥራ እናገራለሁ። መገሠጽስ እግዚአብሔር ገሠጸኝ ለሞት ግን አልሰጠኝም።›› (መዝ. )07.5-08)

# ከፈተና እንዲያድንህ እግዚአብሔርን ጠጥራት

‹‹ሁልጊዜ እግዚአብሔርን በፊቴ አየዋለሁ በቀኜ ነውና አልታወክም። ስለዚህ ልቤን ደስ አለው ምላሴም ሐሴት አደረገች ሥጋዬም ደግሞ በተስፋ ታድራለች›› (መዝ. 06.8-9)

‹‹እኔ ግን ዘወትር ከአንተ ጋር ነኝ፥ ቀኝ እጄንም ያዝኸኝ። በአንተ ምክር መራኸኝ ከክብር ጋር ተቀበልኸኝ። በሰማይ ያለኝ ምንድር ነው? በምድርስ ውስጥ ከአንተ ዘንድ ምን እሻለሁ? የልቤ አምላክ ሆይ፥ ልቤና ሥጋዬ አለቀ እግዚአብሔር ግን ለዘላለም እድል ፈንታዬ ነው። እነሆ፥ ከአንተ የሚርቁ ይጠፋሉና ከአንተ ርቀው የሚያመነዝሩትንም ሁሉ አጠፋኻቸው። ለእኔ ግን ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይሻለኛል መታመኛዬም እግዚአብሔር ነው በጽዮን ልጅ በሮች ምስጋናህን ሁሉ እናገር ዘንድ።›› (መዝ. &2.!3-!8)

‹‹እግዚአብሔር ግን እንደ ኃያልና እንደ ጨካኝ ከእኔ ጋር ነው ስለዚህ አሳዳጆቼ ይሰናከላሉ አያሸንፉም አይከናወንላቸውምና በጽኑ እፍረት ያፍራሉ፥ ለዘላለምም በማይረሳ ጉስቍልና ይጐሰቍላሉ።›› (ኤር. !.01)

‹‹አቤቱ አምላክ ሆይ፥ ተነሥ እጅህም ከፍ ከፍ ትበል ድሆችን አትርሳ። ኃጢአተኛ ስለ ምን እግዚአብሔርን አስቈጣው? በልቡ። አይመራመረኝም ይላልና። አየኸው፥ አንተ ክፋትንና ቍጣን ትመለከታለህና በእጅህ ፍዳውን ለመስጠት ድሀ ራሱን

ለአንተ ይተዋል፥ ለድሀ አደግም ረዳቱ አንተ ነህ።›› (መዝ. 0.02-04)

‹‹ጥሩርና ጋሻ ያዝ፥ እኔንም ለመርዳት ተነሥ። ሰይፍህን ምዘዝ የሚያሳድዱኝንም መንገዳቸውን ዝጋ ነፍሴን፦ መድኃኒትሽ እኔ ነኝ በላት። ነፍሴን የሚሹ ሁሉ ይፈሩ ይጐስቈሉም ክፋትን በእኔ ላይ የሚያስቡ ይፈሩ ወደ ኋላቸውም ይበሉ። ነፍሴ ግን በእግዚአብሔር ደስ ይላታል፥ በማዳኑም ሐሴት ታደርጋለች። አጥንቶቼ ሁሉ እንዲህ ይሉሃል። አቤቱ፥ እንደ አንተ ማን ነው? ችግረኛን ከሚቀማው እጅ፥ ችግረኛንና ድሀውንም ከሚነጥቀው እጅ ታድነዋለህ።›› (መዝ. "5.2-4 ፣ 9-0)

‹‹አቤቱ፥ አንተን ከጥልቅ ጠራሁህ። አቤቱ፥ ድምፄን ስማ ጆሮህ የልመናዬን ቃል የሚያደምጥ ይሁን።›› (መዝ. )!9.1-2)

‹‹ዓይኖቼ ወደ ተራሮች አነሣሁ ረዳቴ ከወዴት ይምጣ? ረዳቴ ሰማይና ምድርን ከሠራ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው። እግርህን ለመናወጥ አይሰጠውም የሚጠብቅህም አይተኛም። እነሆ፥ እስራኤልን የሚጠብቅ አይተኛም አያንቀላፋምም። እግዚአብሔር ይጠብቅሃል፥ እግዚአብሔርም በቀኝ እጅህ በኩል ይጋርድሃል። ፀሐይ በቀን አያቃጥልህም ጨረቃም በሌሊት። እግዚአብሔር ከክፉ ሁሉ ይጠብቅሃል፥ ነፍስህንም ይጠብቃታል። ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም እግዚአብሔር መውጣትህና መግባትህን ይጠብቃል።›› (መዝ. )!.1-8)

# ስለ መንግሥተ ሰማያት ሲሉ የሕይወትን ፈተና መቀበል

ኃይልና ጥንካሬን ያዝ ፤ ልብህንም በሰማያዊው ተስፋ ሙላው። ‹‹ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን የአሁኑ ዘመን ሥቃይ ምንም እንዳይደለ አስባለሁ።›› (ሮሜ. 8.08)

‹‹ከእርሱ ጋር መከራን ከተቀበልን ደግሞ ከእርሱ ጋር እንከብራለን›› ኀዘን ሁሉ ያበቃል ሕመምም ሁሉ ይዋጣል። ፀሐይም በቅርቡ ትወጣለች ፤ ዘለዓለማዊ ሕይወትም መክፈቻ ይሆናል። የተወደዳችሁ ሆይ በተስፋ ጽኑ ፤ ጥንካሬያችሁ እንዲደክምና ጥቃትም እንዲጥላችሁ አትፍቀዱ። ‹‹እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ እናንተ ታለቅሳላችሁ ሙሾም ታወጣላችሁ፥ ዓለም ግን ደስ ይለዋል፤ እናንተም ታዝናላችሁ፥ ነገር ግን ኀዘናችሁ ወደ ደስታ ይለወጣል። ሴት በምትወልድበት ጊዜ ወራትዋ ስለ ደረሰ ታዝናለች፤ ነገር ግን ሕፃን ከወለደች በኋላ፥ ሰው በዓለም ተወልዶአልና ስለ ደስታዋ መከራዋን ኋላ አታስበውም። እንግዲህ እናንተ ደግሞ አሁን ታዝናላችሁ፤ ነገር ግን እንደ ገና አያችኋለሁ ልባችሁም ደስ ይለዋል፥ ደስታችሁንም የሚወስድባችሁ የለም።›› (ዮሐ. 06.!-!2)

‹‹ልባችሁ አይታወክ፤ በእግዚአብሔር እመኑ፥ በእኔም ደግሞ እመኑ።›› (ዮሐ. 04.1)

በዕለት ተዕለት ሕይወታችን የሚያጋጥሙን ሥቃዮች ሁሉ ከሰማያዊው ክብር ብልጭታ ጋር እንኳን እኩል አይደሉም ፤ የዚያ የደስታ ቀን ፀሐይ ስትወጣ የዚህኛው ሕይወት ጨለማ ሁሉ ይጠፋል ፤ እኛም ስቃያችንን ፣ ኀዘናችንን ፣ ሕመማችንንና ለቅሶአችንን ሁሉ አናስታውስም ፤ ለዘለዓለምም ደስታ ይሆናል፡፡ እስራኤላዊያን ከሥቃይ ባርነት ሀገር ሲወጡ ዜማ ዕቃቸውን ይዘው ዘመሩ እንጂ ስቃይና መከራቸውን አላስታወሱም፡፡ (ዘጸ. 05) የጌታችን የብሩህ ፊቱን ክብር ያየ ሰው የሕይወቱን ሥቃዮች ሁሉ ይረሳል፡፡ በምድር ላይ የሚደርሱብን መከራዎችና ሥቃዮች ሁሉ የጌታችንን ፊት አንድ ጊዜ ከማየት ጋር እንኳን እኩል አይደሉም፡፡ ስለዚህ ይህንን ቃልኪዳን አስበህ ጥንካሬህን ይዘህ ጸንተህ ቆይ፡፡ በዚህች ምድር ላይ ጥቂት ሥቃይን ከተቀበልህ በሚመታው ሕይወት ፍጻሜ የሌለው ደስታ ስለሚጠብቅህ ጸንተህ እግዚአብሔርን ተጠባበቀው፡፡

የዚህ ዓለም ሥቃይ የሚቆየው ለጥቂት ጊዜ ብቻ ነው ፤ ለዚህ ሁሉ መጥፎ ነገር ማብቂያ አለው፡፡ መከራዎች ሁሉ የሚያበቁበት ፣ ጊዜው ሲደርስ ሥቃይ ሁሉ የሚያቆምበት ጊዜ ይመጣል፡፡ በሰማያዊው ደስታ ወደ ተዘጋጀው ክብር ተመልከት፡፡ ለዚያ ክብር ስትልም በዚህ ሕይወት የሚገጥምህን መከራ ሁሉ በጽናት ተቀበል፡፡ ስለ ክርስቶስ ስትል ፈተናዎችን ሁሉ ተቋቋመህ ተቀበል ፤ የዕረፍት ጊዜም ቶሎ እንደሚመጣ ዕወቅ ፡- ‹‹ስለዚህም አንታክትም፥ ነገር ግን የውጭው ሰውነታችን ቢጠፋ

እንኳ የውስጡ ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል፡፡ የማይታየውን እንጂ የሚታየውን ባንመለከት፥ ቀላል የሆነ የጊዜው መከራችን የክብርን የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ ያደርግልናልና ፤ የሚታየው የጊዜው ነውና ፥ የማይታየው ግን የዘላለም ነው፡፡›› (2ቆሮ. 4.06-08)

‹‹ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን በመነሣቱ ለሕያው ተስፋና ለማይጠፋ፥ እድፈትም ለሌለበት፥ ለማያልፍም ርስት እንደ ምሕረቱ ብዛት ሁለተኛ የወለደን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ፤ ይህም ርስት በመጨረሻው ዘመን ይገለጥ ዘንድ ለተዘጋጀ መዳን በእምነት በእግዚአብሔር ኃይል ለተጠበቃችሁ ለእናንተ በሰማይ ቀርቶላችኋል፡፡ በዚህም እጅግ ደስ ይላችኋል፥ ነገር ግን በእሳት ምንም ቢፈተን ከሚጠፋው ወርቅ ይልቅ አብልጦ የሚከብር የተፈተነ እምነታችሁ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ፥ ለምስጋናና ለክብር ለውዳሴም ይገኝ ዘንድ አሁን ለጥቂት ጊዜ ቢያስፈልግ በልዩ ልዩ ፈተና አዝናችኋል፡፡›› (1ጴጥ. 1.5-7)

‹‹ወዳጆች ሆይ፥ በእናንተ መካከል እንደ እሳት ሊፈትናችሁ ስለሚሆነው መከራ ድንቅ ነገር እንደ መጣባችሁ አትደነቁ፤ ነገር ግን ክብሩ ሲገለጥ ደግሞ ሐሤት እያደረጋችሁ ደስ እንዲላችሁ፥ በክርስቶስ መከራ በምትካፈሉበት ልክ ደስ ይበላችሁ፡፡ ስለ ክርስቶስ ስም ብትነቀፉ የክብር መንፈስ የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ላይ ያርፋልና ብፁዓን ናችሁ፡፡›› (1ጴጥ. 4.02-04)

‹‹በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፤ ከተፈተነ በኋላ ለሚወዱት ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸውን የሕይወትን አክሊል ይቀበላልና፡፡›› (ያዕ. 1.02)

‹‹እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ በጎ ወታደር ሆነህ፥ አብረኸኝ መከራ ተቀበል፡፡ የሚዘምተው ሁሉ ለጦር ያስከተተውን ደስ ያሰኝ ዘንድ ትዳር በሚገኝበት ንግድ ራሱን አያጠላልፍም፡፡ ደግሞም በጨዋታ የሚታገል ማንም ቢሆን፥ እንደሚገባ አድርጎ ባይታገል፥ የድሉን አክሊል አያገኝም፡፡ የሚደክመው ገበሬ ፍሬውን ከሚበሉት መጀመሪያ እንዲሆን ይገባዋል፡፡... ብንጸና፥ ከእርሱ ጋር ደግሞ እንነግሣለን፤ ብንክደው፥ እርሱ ደግሞ ይክደናል፤›› (2ጢሞ. 2.3-6 ፣ 02)

‹‹ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ፥ ወይስ ጭንቀት፥ ወይስ ስደት፥ ወይስ ራብ፥ ወይስ ራቁትነት፥ ወይስ ፍርሃት፥ ወይስ ሰይፍ ነውን? ስለ አንተ ቀኑን ሁሉ እንገደላለን፥ እንደሚታረዱ በጎች ተቆጠርን ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው፡፡ በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን፡፡ ሞት ቢሆን፥ ሕይወትም ቢሆን፥ መላእክትም ቢሆኑ፥ ግዛትም ቢሆን፥ ያለውም ቢሆን፥ የሚመጣውም ቢሆን፥ ኃይላትም ቢሆኑ፥ ከፍታም ቢሆን፥ ዝቅታም ቢሆን፥ ልዩ ፍጥረትም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ፡፡›› (ሮሜ 8.''5-''9)

# ሥነ ምግባርና መልካም ጠባይ

## ክርስቲያን እንዴት መኖር ነው ያለበት?

በጠባይህና በአነጋገርህ ሁሉ ሥነ ምግባር ያለውና ተግባቢ ሁን ፤ ሌሎችን የሚፈትን አንዳች ነገርም አታድርግ። በምግባርህ ሁሉ ፍጹም ምሳሌና መልካም መሪ ሁን። ይህም ሌሎችን ለማስተማር ይረዳሃል። ሁልጊዜ ትሑት ፣ ፈገግተኛ ፣ መልካም ፣ ሰላማዊና ፍጹም ሁን ምክንያቱም የአንድ ሰው ውጪአዊ የመልካምነት ገጽታው የውስጣዊ መልካም ገጽታው ማሳያ ነው። ይህን ካደረግህ የክርስትናን ሃይማኖት ንጽሕና እንደሚያንጸባርቅ ሰባኪ ትሆናለህ።

ለምሳሌ በጥንቱ የክርስቲያኖች ዘመን አንድ እምነት የለሽ ሰው የእርሱ ቢጤ የሆነን ሌላ እምነት የለሽ ሰው ሲያገኘው ጥሩ ጠባይ እና ሥነ ምግባር ያሳየዋል። ይህንን አይቶም ‹‹ስትመጣ መንገድ ላይ ክርስቲያን አግኝተህ ነበር?›› ብሎ ጠየቀው። ይህም ሆነው የክርስቲያኖች ገጽታና ጠባያቸው መልካምና ፣ የተረጋጋ ፣ ሰላማዊ ስለነበር ነው። ይህንንም ገጽታቸውን ሰዎች አይተዋቸው ብቻ እስኪረዱት ድረስ ይንጸባረቅ ነበር። ታዲያ አንተስ ለምን የእነሱን ፈለግ አትከተልም? በሔዱበት የፍጹምነት አቅጣጫስ ለምን አትራመድም? ብረት ቃጭል የሚታወቀው በሚያሰማው ድምጽ ነው ፤ አንተም በጠባይህና በአኗኗርህ ከእስራኤል መንጋ የተለየህ አትሁን።

በዚህም ሕይወት ሆነ በሚመጣው ሕይወት ሰው ልጅ መለኪያው ያጠራቀመው ገንዘብ መጠን ፣ ያገኘው ሥልጣን ፣ ያገኘው ዝና እና መዓርግ አይደለም። መለኪያው ሥነ ምግባሩና የነፍሱ የመልካምነት ደረጃ ነው። የዚህም ምሳሌ የሚሆኑት ትሕትና ፣ ሌሎችን መርዳት ፣ መልካም ጠባይ ፣ ንጹሕ ልብና ንጽሕት ነፍስ ናቸው።

በአንተ ውስጥ ለው መልካምነት ተፈጥሮህ ይሁን እንጂ አታስመስል። የሐሰትንም ልብስ አትልበስ ፤ አንድ ሰው ምንም ያህል መጥፎ ጠባዩን ለመሸሸግ ቢሞክር ከብዙዎች ተደብቆ አይቀርም ፤ ይገለጣል እንጂ። ከሰዎች ሁሉ ለመደበቅ ብትችል እንኳን ከእግዚአብሔር ግን ልትደብቀው አትችልም። ውጪህ ውስጣዊ ማንነትህን ይናገራል ፤ በፊትህም ላይ ይንጸባረቃል። መልካምም ሆነ ክፉ ጠባይ ቢኖርህ ሁሉም ሰው ዓይኖችህን በማየትና ገጽታህን በማጥናት ሰዎች ሊያውቁህ ይችላሉ። በኮሽታ ብቻ መልካምነትህን ልትናገር ትችላለህ። ውጪአዊ ገጽታህን ብቻ በመመልከት ሰዎች ጠባይህን ሊናገሩ ይችላሉ።

መንፈስ ቅዱስ በጠቢቡ አንደበት እንዲህ ይላል ‹‹ምናምንቴ ሰው የበደለኛም ልጅ በጠማማ አፍ ይሄዳል ፤ በዓይኑ ይጠቅሳል፥ በእግሩ ይናገራል፥ በጣቱ ያስተምራል ፤ ጠማማነት በልቡ አለ፥ ሁልጊዜም ክፋትን ያስባል ጠብንም ይዘራል።›› (ምሳ.6.02-04)

ልብ በሮች እንዳሉት ዕወቅ ፤ ተጽእኖዎችም በበሮቹ በኩል ይገባሉ፡፡ እነዚህ በሮች ሕዋሳት ናቸው፡፡ ያለ ሕዋሳት ነፍስ ምንም ነገርን መለየት አይቻላትም ፤ ስለዚህ የምታየው የምትሰማው ፣ የምታሽትተው ፣ የምትዳስሰው ነገር ቶሎ ይሰማሃል፡፡ በተለይም የምትሰማቸውና የምታያቸው ነገሮች በነፍስ ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ አለ ፤ የምታያቸውና የምትሰማቸው ነገሮችም ፈጥነው ወደ ልብህ ይደርሳሉ፡፡ በዚህም የተነሣ የምታየውና የምትሰማው ነገር መልካም ከሆነ በነፍስህላይ ይንጸባረቃል፡፡ በአንጻሩ ሕዋሳትህ መጥፎ እይታንና መጥ ድምጽን ወደ ልብህ ካስገቡ በልብህ ወስጥ ይቀረጽብሃል፡፡ ይህም ማለት ልክ በሩ ሁልጊዜ እንደተከፈተና ከውስጥም ከውጪም አቧራ ፣ ነፋስና ሌሎች ነገሮችን ያለ አንዳች ክልከላ የሚያገባ ቤት መሆን ማለት ነው፡፡ ወደ ልብህ መጥፎ እይታዎችንና ክፉ ሃሳቦችን እንደ ልብ እያስገባህ ውስጥህ ደህንነት ሊሰማው አይችልም፡፡ ነፍስህ ሁልጊዝ ትታወክና ትጨነቃለች እንጂ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ በሰላምና በጸጥታ ልትኖር አትችልም፡፡ ስለዚህ ነፍስህን ጠብቅ ፣ ሕዋሳቶችህም ቆሻሻና ክፉ የሆነን ነገር አለመቀበላቸውን አረጋግጥ፡፡

ምግባረ ሠናይ ሁን ፤ ሁሉንም ሰው አክብር ፤ መልካም ልማዶችንም ያዝ ፣ ከተናቁ ነገሮች ተርታና ከክፉ ልማዶችም ሽሽ፡፡ ከሰዎች ጋር ባለህም መስተጋብር ደስተኛ ሁን ፤ መጨነቅንም አትውደድ፡፡ አትኮሳተር ፤ እንዲህ ካደረግህ በዙሪያህ

ያሉትን ሰዎች አትረብሽም፡፡ ያለ ቁጣና ብስጭት ሥራህን በአግባቡ ተወጣ፡፡ በንግግሮችህና በጠባይህ ሁሉ ከክፋት ራቅ፡፡ ኅሊናህን ንጹሕ አድርገህ ጠብቅ ፤ ጻድቃንን ብቻም አስብ፡፡

# ትሕትናና የዋህነት

ትሕትና ከመልካምነት ሁሉ ያማረ ፣ ውድና ታላቅ መልካምነት ነው። ትምክህትና ኩራት ደግሞ መጀመሪውን የሰው ልጅ ውድቀት ያስከተለ የክፋት ሁሉ መንሥኤ ነው።

ትሕትና ፍቱን መድኃኒት ነው። ስለ ትሕትና ለማወቅ ትፈልጋለህ? እንደዚያ ከሆነ ራስህን እወቅ ፣ ራስህንም መርምር። እንደ እውነቱ ከሆነ አንተ ምንም ነህ ፣ ለምንም የማትገባም ነህ ፤ ያሉህ ጸጋዎችና ተሰጥኦዎች ሁሉ ከእርሱ ናቸውና ሁሉም ነገርም ከእርሱ ነውና በአንተ መመካት ምክንያት ለእግዚአብሔር የሚገባውን ክብር አትስረቅ።

በአንተ ዘንድ ብርሃን ቢኖር ከራስህ ዘንድ እንዳይመስልህ ፣ ይህንን ጸጋ ካደለህ ከብርሃን ምንጭ ነው እንጂ።

ትሕትና የበጎነቶች ሁሉ እናት ናት። ፍቅር መሠረት ፣ ጸጥታ ወደብ ፣ ወደ ፍጹምነት መወጣጫ ገመድ ፣ የቁጣ ማብረጃ ፣ የመንፈስ ማረጋጊያናሰላም ወደ ነፍስ የምትገባበት በር ትሕትና ነው።

ትሕትና የመታዘዝ መሠረት ፣ የጥበብ ሁሉ ፍጻሜ ፣ የክርስቲያን ነፍስ ብርህት እንድትሆን ኀሊናም የሚያበራበት መንገድ ነው።

ትሕትና ሊወሰድ ወይም ሊሰረቅ የማይችል በጥበብ የተሞላ ሀብት ነው። የበጎነት ሁሉ በር ፣ የሰላምና የጸጋ ሁሉ

ቁልፍ ፣ የፍጹምነት መክፈቻ ፣ የዕርቅና ሰላም ማሰሪያ ፣ ፍቅርን ጠብቆ ማቆያ ፣ ለኅሊና በሚሆን ሰላም የተሞላ መርከብ ፣ ሁሉም በጎነቶች ምንጭ ነው፡፡

ትሕትናን ተማር ያን ጊዜ ነፍስህ በቅድስና ታድጋለች፡፡ ትሑት ከሆንህ እግዚአብሔርን ሕግጋትና ትእዛዛት ሁሉ ያለ አንዳች ድካምና ጭንቀት ትጠብቃለህ ፤ እምነትህ ጠንካራ ተስፋህም ጸና ይሆናል፡፡

ከአፈር እንደተፈጠርህና ወደ አፈርም እንደምትመለስ አስታውስ፡፡ (ዘፍ. 3.09)

ስለዚህ ተስፋህ ሁሉ ያለህን ነገር ሁሉ በእርሱና ከእርሱ በተቀበልከው በእግዚአብሔር ላይ አድርግ፡፡

ፍቅር ከትሕትና ጋር ሲሆን በሌሎች መልካም ነገርና ስኬት እንድትደሰት ስለሚያደርግህ ትሕትናህ ያለ ማስመሰልና ሽንገላ እውነተኛ የእግዚአብሔር ወዳጅ እንድትሆን ያደርግሃል፡፡

በትሕትና ውስጥ የራስን ድካምና በደል ማስታወስ እንጂ በሌሎች ጸጋና መልካም ነገር መቅናት ፣የሌሎችን ስኅተት መንቀስና ስለ ውድቀታቸው መንቀፍም የለም፡፡ ትሑት ከሆንህ ሰዎችን ከልብህ ትወድዳለህ ፣ ታከብራለህ ፣ በጥሩ ሁኔታም ትግባባቸዋለህ ፤ ያለቁጣና ጠብ በሰላም ከሁሉ ጋር ትኖራለህ፡፡ አንተ ተረስተህ ሌሎች ከዝና ጫፍ ሲደርሱ ወይም ሌሎች ከፍ ያለ የሥራ ሓላፊነት ኖሮአቸው የአንተ ዝቅተኛ ሲሆን ትሕትና ካለህ አትረበሽም፡፡

በመከራ ስትፈተን በትዕግሥት ሥቃይን ትቋቋማለህ ፤ ራህን እየወቀስህም ትጸጸታለህ ፤ የሚደርስብህም መከራ እንደሚገባህ አምነህ ትቀበላለህ፡፡

ትሑት ከሆንህ ሳትቆጣና ሳትታወክ ሁሉን በጸጥታና በእርጋታ ትቋቋማለህ፡፡ ከነቢዩም ጋር አብረህ እንዲህ ትላለህ፡፡ ‹‹እኔ ግን ወደ እግዚአብሔር እመለከታለሁ፥ የመድኃኒቴንም አምላክ ተስፋ አደርጋለሁ አምላኬም ይሰማኛል፡፡ ጠላቴ ሆይ፥ ብወድቅ እነሣለሁና፥ በጨለማም ብቀመጥ እግዚአብሔር ብርሃን ይሆንልኛልና በእኔ ላይ ደስ አይበልሽ፡፡ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ሠርቻለሁና እስኪምዋገትልኝ ድረስ፥ ፍርድን ለእኔ እስኪያደርግ ድረስ ቍጣውን እታገሣለሁ፡፡ ወደ ብርሃን ያወጣኛል፥ ጽድቅንም አያለሁ፡፡›› (ሚክ. 7.7-9)

የዋህነት ግጭትን ስለማይቀበል ፤ ትሕትናም ከጠብ ስለሚያሸሽ ትሑት ከሆንህ ሰላምን ፣ ምቾትን ፣ እርጋታን ታገኛለህ፡፡ ‹‹በትዕቢት ጠብ ብቻ ይሆናል ጥበብ ግን ምክርን በሚቀበሉ ዘንድ ናት፡፡›› (ምሳ. 03.0) ‹‹የዋሆች ብፁዓን ናቸው፥ ምድርን ይወርሳሉና፡፡›› (ማቴ. 5.5)

ትሕትና የሚባለው ሰው ‹የተዋረድሁና ዝቅ ያሁ ነኝ!› ሲል ወይም ደግሞ ያደፈ ልብስ ሲለብስ ወይም ዝቅተኛ ሥራዎችን ሲሠራ እንዳይመስልህ፡፡ ትሕትና ይህ ቢሆን ኖሮ ሁሉም ሰው ትሑት መሆን ይችል ነበር፡፡

ትሕትና ማለት ረጋ ማለትና ድምጽን ቀንሶ መናገር ፣ ማቀርቀር እንዳይመስልህ ትሕትና ማለት ስለ እግዚአብሔር ብለህ መዋረድን ለመቀበል የምታሳየው ጥንካሬ ፣ በደለኛ መሆንህን አውቀህ በመጸጸት መከራዎችን በትዕግሥት መቋቋምህ ነው ፤ ይህን ማድረግ ከቻልህ እውነተኛ ትሑት ልትሆን ትችላለህ፡፡ ራስህን መርምር ፤ አንተ ማነህ? አሁን ምንድር ነህ? ኋላስ ምን ትሆናለህ? እኛ ከንቱና ኢምንት እንደሆንን አታውቅም? ተፈጠርኸው ከአፈር ነው ፣ አሁንም ሥጋህ በቆሻሻ ተሞልቷል ፣ ነፍስህም በትልቅ ሽክም ደክማለች፡፡ አበቦችንና ዛፎችን አተኩረህ ተመልከታቸው ፤ ከአንተ ሰውነት ይልቅ የተዋቡ ናቸው፡፡ ዛፎች ቅባትን ፣ ጣፋጭ ፍሬዎችን እና መልካም መዓዛን ያስገኙ የለምን? የአንተ ሰውነት ግን እድፍና ቆሻሻን ያወጣል፡፡ የሕይወትህን ፍጻሜ አስብ ፤ ሰውነትህ ወደ ትቢያና አመድ የሚቀየር አይደለምን? ‹‹ሕይወታችሁ ምንድር ነው? ጥቂት ጊዜ ታይቶ ኋላ እንደሚጠፋ እንፍዋለት ናችሁና፡፡›› (ያዕ. 4.04)

ሰውነትህን ተመልከት ፤ ‹‹እንደሚጠፋ የሣር አበባ›› ሆኖ ታገኘዋለህ፡፡ (ያዕ. 1.0)

ዓለማዊ ምኞቶችህ ተስፋ ሳይኖራቸው ወደ መቃብር እንደሚወርዱ አስብ፡፡ አዕምሮህን ልብ ብለህ መዝነው ደካማና ሁሉን ነገር መረዳትና ማስታወስ የማይችል ደካማ ሆኖ

ታገኘዋለህ፡፡ ልብህንም ፈትሸው ፤ ባዶ ፣ ወናና ሀኬተኛ ሆኖ ታገኘዋለህ፡፡

ስሜትህንም ፈትሽ ፤ ደካማ ሆኖ ታገኘዋለህ፡፡ በአንተ ውስጥ ያለው ነገር ሁሉ የተናቀና ምንም ሊከበር የማይገባው እንደሆነ ትረዳለህ፡፡

በዚህች ሕይወት አንተ በነፋስ እንደሚነዳ ቅጠል ፣ በአየርም ላይ እንዳለ ላባ ነህ፡፡ አንድ ጊዜ በፈተናዎች ትጎዳለህ ፣ ልላ ጊዜ ደግሞ በመከራና ችግር ታዝናለህ ፣ በሦስተኛው ጊዜ በቁጣ ትነድዳለህ ፣ በአራተኛው ደግሞ በኃጢአት ትማረካለህ፡፡ አንዴ በትዕቢት ስትኮፈስ ፣ በፍርሃት ሲውጥህ ፣ በጭንቀት ስትታወክ ፣ አንዴ ምኞትህን ስትከተል ትኖራለህ፡፡

ስለዚህ ሕይወትህ የሕመምና የምጥ መፈራረቅ ነው፡፡ እንዲህ ያለ ሰው ምንኛ ደካማና ምስኪን ነው? እርሱ ደካማ ባሪያ ፣ የምኞቶቹና የልማዶቹ እስረኛ ፣ ለፈቃዱ ተገዢ ሆኖ እያለ ራሱን አንዳች አድርጎ የሚያስብ ትምክህተኛና ትዕቢተኛ ነው፡፡ ‹‹በጌታ ፊት ራሳችሁን አዋርዱ ከፍ ከፍም ያደርጋችኂል፡፡›› (ያዕ. 4.0)

‹‹ሰው ሳይወድቅ በፊት ልቡ ከፍ ከፍ ይላል፥ ትሕትናም ክብረትን ትቀድማለች፡፡›› (ምሳ. 08.02)

‹‹እነዚህን ሁሉ እጄ ሠርታለችና እነዚህ ሁሉ የእኔ ናቸው ይላል እግዚአብሔር ነገር ግን ወደዚህ ወደ ትሑት፥

መንፈሱም ወደ ተሰበረ፥ በቃሌም ወደሚንቀጠቀጥ ሰው እመለከታለሁ።›› (ኢሳ. %6.2)

‹‹ለዘላለም የሚኖር ስሙም ቅዱስ የሆነ፥ ከፍ ያለው ልዑል እንዲህ ይላል። የተዋረዱትን ሰዎች መንፈስ ሕያው አደርግ ዘንድ፥ የተቀጠቀጠውንም ልብ ሕያው አደርግ ዘንድ፥ የተቀጠቀጠና የተዋረደ መንፈስ ካለው ጋር በከፍታና በተቀደሰ ስፍራ እቀመጣለሁ።›› (ኢሳ. $7.05)

ትሑት ሰው ራሱን በናቀ እና ትንሽነት በተሰማው ቁጥር እግዚአብሔርን ያከብራል ፤ እግዚአብሔርም ከፍ ከፍ ያደርገዋል። እግዚአብሔር የሚያከብሩትን ያከብራልና ትሑት ሰው ላለመከበር ቢሸሽም እንኳን ክብር ይከተለዋል።

ትሕትና ልክ እንደ በጎ መዓዛ ነው። በጠበቅሽውና በሰወርከው ቁጥር የሚጣፍጥና ሽታው የሚዳረስ ይሆናል። ቅድስት ድንግል ማርያም እንዳለችው ‹‹ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች፥ መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች፤ የባሪያይቱን ውርደት ተመልክቶአልና። እነሆም፥ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል፤›› (ሉቃ. 1.#6-#8)

ትሕትና ሀናንን ከፍ ከፍ አደረጋት ፣ ዳዊትን በእስራኤል ዙፋን ላይ አስቀመጠው ፣ አስቴርን የአርጤክስ ሚስት አደረጋት ፣ ያዕቆብን ከወንድሙ ኤሳው በላይ ከፍ አደረገው ፣ ቅዱሳንም ሁሉ በትሕትና ከፍ ከፍ አሉ።

# ትሕትናን ለሚሹ ሁሉ የተሰጠ ምክር

ከንቱ ውዳሴን ለማስቀረት የሠራኸውን መልካም ነገር ለሌሎች አትግለጥ። ሰዎች አስተያየት እንዲሰጡህ በሚጋብዝ መንገድ አንዳች ነገር አታድርግ ወይም አትናገር ፤ ይህን ካደረግህ ጌታህ ‹‹ዋጋህን ተቀብለሃል!›› ይልሃል። (ማቴ. 6.2) ይልቅስ ወደ ኩራትና ትምክህት ከሚመራህ ነገር ሁሉ ሽሽ።

ትሕትናን ውደድ! የትምክህትና የኩራት መንሥኤዎች ሲከስሙ ደስ ይበልህ! ሰዎች እንዲያሞግሱህም አትመኝ።

ሰዎች ሲያሞግሱህ ትሕትናህን ለመጨመር ምክንያት አድርገው ፤ ሌሎችን በማመስገንም ደስ ይበልህ!

በሰዎች ላይ አትመቀኝ ፤ ነገር ግን የተቀደሰ ቅናትን ገንዘብ አድርግ ፤ ዓላማህ ሰዎችን ማስደሰት አይሁን ፤ እግዚአብሔርን ደስ ስታሰኝ ግን ሰዎች ይረካሉ። ጥረትህ ሁሉ እግዚአብሔርን ለማክበር /ከፍ ከፍ ለማድረግ/ ይሁን። ‹‹ሁሉ ከአንተ ዘንድ ነውና፥ሁሉ ከእጅህ የመጣ ነው፥ ሁሉም የአንተ ነው።›› እያልህ ክብርን ሁሉ ለእግዚአብሔር ብቻ ስጥ እንጂ በሥራዎችህ እንዲታበይ ለልብህ አትፍቀድለት። (1ዜና !9.04-06)

ልብህ ለከንቱ ውዳሴ ፣ ለመታበይና ለመመካት ያለውን ምኞት አውጥተህ ጣል!

በዚህች ምድር ላይ ያለህ ነገር ሁሉ ከአንተ እንዳልሆነ ከ‹‹ብርሃናት አባት›› ከእግዚአብሔር እንደሆነ አውቀህ ያለህን ነገር ሁሉ ከአጠገብህ ላለው አትከልክል፡፡ (ያዕ. 1.07)

ልብህን ትሑትና የዋህ አድርገው ፤ የዋህና ለስላሳ ሁን እንጂ ወደ ክፋትና መራገም አትመለስ፡፡ በመሸሽ ወይም በመታገሥ ወይም ጸጥ በማለት ፣ ወይም መልካም ቃላትን በመናገር ከሌሎች ግፉነት ራስህን አድን፡፡ ለሁሉም ሰው ትሑት ፣ የተረጋጋና የዋህ ሁን ፤ የዋህነትህንም ከደካማነት ነጻ አድርገው፡፡

ከወንድሞችህና ከእኅቶችህ ጋር በፍቅር ተመላለስ ፤ በትሕትናና በየዋህነትም ቅረባቸው፡፡

ታዛዣቸው ሁን ፣ በወዳጅነት መንፈስ አነጋግራቸው ፣ በፈገግታም አዋራቸው፡፡ ለእነርሱ ከልብ የሆነ አክብሮት ይኑርህ ፣ የሚገባ ክብርና ስፍራንም ስጣቸው፡፡ በትሕትናና በየዋህነትም ምሳሌ ሁናቸው፡፡ እግዚአብሔር የሚወድደው መሆኑን አውቀህ በትዕግሥት እንዲያጸናህ ሁሉን ከአምላካዊ እጆቹ ተቀበል፡፡

ትሕትና ከእውቀት ይበልጣል፡፡ ትንሽ እውቀት ያለው ትሑት ደሃ ከሚኩራራና ከሚታበይ ሀብታም ፈላስፋ እጅግ ይሻላል፡፡

የጥሩነትን ሕይወት ለመኖር ሙሉ መድከም ደግነት ከሌለበት ብዙ እውቀት ይሻላል፡፡ መልካምነት ከእውቀት ይልቅ እጅግ ከፍ ያለና የሚማርክ እንደሆነ እወቅ፡፡

ትዕቢተኛ በሰውና በእግዚአብሔር የተጠላ ነውና ልብህን እንዲታበይ አትተወው፡፡ በእውቀትህ አትታበይ ፣ በእጅህም ሥራ አትመካ ይልቅስ ትሑት ሆኖ መኖርን ተማር፡፡ በእግዚአብሔር ጸጋ እንጂ በአንተ ኃይና ጥንካሬ አንዳች ልትቀበል እንደማይቻልህም እወቅ!

እውቀትና ብልሃትን ያገኘህ መስሎ ከተሰማህ ያላየሃቸውና የማታውቃቸውን ብዙ ነገሮች አስተውለህ ተመልከት፡፡ አእምሮህ በሳይንስና በብዙ እውቀት ቢሞላ እንኳን እጅግ ጥልቅና ሰፊ ከሆነው እውቀት ገና ዳርቻው ላይ እንዳለህ እመን፡፡

አለማወቅህንና የእውቀትህን ውስንነት እመን ፤ ፈጽሞ ራስህን አንዳች አድርገህ አትቁጠር፡፡ ስለሌሎች በጎ በጎውን አስብ የላቀ ጥበብና ከፍተኛ መልካምነትም ይህ ነው፡፡ ምን እንደሚጥልህ አታውቅምና አንድ ሰው ሲወድቅ ስታይ ራራለት ፣ እግዚአብሔር ፈጥኖ እንዲያነሣውም ለምንለት፡፡

መልካም ሰው ሆነህ የምትቆይ መሆንህን ወይም ደግሞ በፈተና የምትወድቅ መሆንህን ፈጽመህ አታውቅምና አንድ ሰው ትልቅ በደል ሲፈጽም ስታይ ራስህን ከእርሱ የሚሻል አድርገህ አትቁጠር፡፡ ሁላችንም ደካሞችና ከትዕቢት ወጥመድ እንዲጠብቀን የእግዚአብሔርን እርዳታ የምንፈልግ ነን፡፡

አንዳች ስኅተት በራስህ ላይ ስታገኝ ፣ ወይም መስተካከል ያለበት ነገር ሲኖርህ ትምክህትህና ኩራትህ እንዳትታረምና እንዳትታደስ እንዲያደርግህ አትፍቀድለት፡፡

የሌሎችን ምክር ከምስጋና ጋር ተቀበል ፤ ራስህን ለማረም ተጠቀምበት፡፡ ሌሎችንም ስትመክር በፍቅር ፣ በትሕትናና በየዋህነት ይሁን፡፡

ክርስትና የዋህ ፣ ርኅሩኅ ፣ ለስላሳ ፣ የተረጋጋና ደስተኛ እንደሚያደርግ እያሳየህ ለሌሎች ምሳሌ ሁን፡፡

ለትንሽ ትልቁ ትሑት ሁን፡፡ በእግዚአብሔርና በሰው ዘንድ የተወደድህ እንድትሆን የተረጋጋህ ሁን፡፡ አንድ ትልቅ ነገር ባገኘህ ጊዜ አትደነቅ ፤ ይልቅስ ጸጋውን ላደለህ ፣ ያንን ቸርነትም ላጎነጸፈህ ለእግዚአብሔር ክብርን ስጥ፡፡

ባማረ ገጽታህ ወይም በወጣትነት ጉልበትህ አትመካ ፤ ሁለቱም ይጠፋሉና፡፡ ትንሽ ሕመም የፊትን ውበት ያጠፋል ፣ የሰውን ኃይልም ያጠፋል፡፡

በሀብትህም አትመካ ፤ ሊወሰድ ፣ ሊጠፋ ወይም ሊሰረቅ ይችላልና፡፡

የከበሩና ኃያላን ወዳጆችህንና ዘመዶችህን አታሳይ ፤ ትምክህትህንም የእርሱ ለሆኑት ሁሉን በሚሰጠው በእግዚአብሔር ላይ አድርግ፡፡

ራህን ከሌሎች እንደሚሻል አድርገህ አትቁጠረው ፤ ይህ ከሆነ በሌሎች ዓይን የተናቅህ ትሆናለህ፡፡ ራስህን ከሁሉ በታች አድርገህ አስብ ይህ ካልሆነ እግዚአብሔር ይጥልሃል ፤ ሰዎችም ይሰርዙሃል ፣ከልባቸውም አውጥተው ይጥሉሃል፡፡ አንዳች መልካም ነገር ካለህ ወይንም ካገኘህ ሌሎች ከአንተ የተሻለ እና

የሚበልጥ ነገር እንዳላቸው አስብ፡፡ የምትታበይና የምትመካ ከሆንህ አይሳካልህም ፣ ብስጩም ትሆናለህ ፤ ትሑትና የዋህ ከሆንህ ግን ሁሉም ይከናወንልሃል፡፡ ከከበሩ እና ከገነኑ ሰዎች ጋር መታየትን አትውደድ ፤ ከትሑታንና ከምስኪኖች ጋር ሁን ፤ ከመካከላቸውም በመሆን ደስ ይበልህ፡፡

ከዕባብ የምትሸሸውን ያህል ከግብዝነት ሽሽ ፤ ከልብህም አውጥተህ ጣለው፡፡ ውጪህ እንደ ውስጥህ ይሁን ፤ ‹የሚያደባ› ‹የሚያታልል› ‹ግብዝ› እንዲሆን ለልብህ አትፍቀድለት፡፡ በእግዚአብሔር ፍጥረት ላይ ፈራጅ እንደሆንህ ይቆጠርብሃልና ትንሽና ያረጀ ፣ ደሃ ብለህ ማንንም አትናቅ ፣ አታንቋሽሽ፡፡

ሁሉን ሰው አክብር ፣ ስሜታቸው እንዳይጎዳም ጠብቅላቸው፡፡ በመንገድ ላይ አካል ጉዳተኛ ስታይ ወደሚፈልግበት ምራው፡፡ መልካም ሥራን ትንሽ ነገር ነው ብለህ ራስህን ከትሕትናና በጎነት አታርቅ፡፡ ጌታህ ሊያገለግል እንጂ ሊገለግሉት እንዳልመጣ በመረዳት ሌሎችን በማገልገል መልካም ምሳሌ ሁን፡፡ (ማቴ. !.!8)

ሕሙማንንና እስረኞችን ጠይቅ፡፡ ድሆችና መጻተኞችንም ተቀበል፡፡ ደካማውን እርዳው ፤ ያዘነውንም አጽናናው፡፡ የተሰበረውን አጽናው (አበርታው) በአደጋ ላሉትም መጠጊ ሁናቸው፡፡ ለድሃው ርኅሩኅ እና ታጋሽ ሁንለት፡፡ የሚጎዱህንም ሰዎች ይቅርታ ጠይቃቸው፡፡

የሚያሰቃዩህን ሰዎች መርቅ ፤ የሚጠሉህንም ውደድ፡፡ አንድ ሰው ቢንቅህ ወይም ቢሰድብህ ደስ ይበልህ ሐሴትንም አድርግ፡፡ ዋጋህ በሰማያት እጥፍ እየሆነ ነውና፡፡

# የትምክህት መጥፎነት

ትምክህት የመርዝ ተክል ፣ ቅናትን ፣ ጥላቻንና በቀልን የሚያስከትል ወረርሽኝ ነው። የእግዚአብሔርን ክብር የሚነጥቅ የማይታይ ሌባ ነው። በሰውና በእግዚአብሔር ፊት የተናቀ የዲያቢሎስ ግኝት ነው።

ትምክህት የክፉት ሁሉ መነሻ ነው። ትምክህት ወደ ሲኦል ከሚጋልብ ፣ እግዚአብሔርን በማምለክ ደካማ ከሆነ ፣ ርኵሰትን ከሚወድ ፣ ከበጎነት ውጪ ከሆነ ከእግዚአብሔር ከራቀ ትዕቢተኛ ልብ የሚመጣ ነው።

ትምክህት አንድን ሰው የሌሎችን ጉድለት የሚነቅስ እንዲሆን ያደርገዋል። ይህ ደግሞ የልብ መቆሸሽ ምልክት ፣ በነፍስ ላይ እንከን የመኖሩና ከእግዚአብሔር ጸጋ የመለየት ማሳያ ነው።

እንዴት ያለ አስከፊ በደል ነው! ምን ያህልስ አስቀያሚ ነው! በጎነትን ሁሉ የሚያጠፋ ተናካሽ አውሬን ይመስላል። ትምክህት የበላይነትን ለማግኘት እንደ እሳት መንደድ ፣ የክብርንና የግርማ ሞገስን ጥም ለማርካት መጋለብ ነው።

ትምክህት መልአክንስ የጣለ አልነበረም? ‹‹አንተ የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ ሆይ፥ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ!›› (ኢሳ. 04.02) ለአምላክነት ጓጉቶ ለጠላት በታዘዘስ ጊዜ አዳምን ያዋረደውና ከጸጋው ያራቆተው ራስን ከፍ አድርጎ የማሰብ

አልነበረምን? ሀገራትን ያወደመ ፣ መንግሥታትን ገለበጠ ፣ ዙፋናትንም ያጠፋ ትምክህት አይደለም እንዴ? ብዙ የተከበሩና የተመሰገኑ ሰዎችን ትምክህታቸው የቀንን ብርሃን እና የፀሐይን መውጣት ማየት እንደማይችሉ ሌሊት ወፎች ሲያደርጋቸው አላያችሁም? እንዲጅ ላሉት ሁሉ በትምክህታቸውና በመኩራራታቸው ምክንያት ከሥልጣናቸውና ከደረጃቸው ተዋርደው ሥልጣንና መዐርጋቸው ጠፍቶ ትዝታ ሆኖባቸዋል።

እንደ ነገርኳችሁ ትምክህት የእግዚአብሔር የሆነውን ሰርቆ ለተናቀውና ለተዋረደው ለሰው ልጅ የሚሰጥ ቀማኛ ነው። ትምክህት የእግዚአብሔርን ክብር ለመጋራት ይወዳል። ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልከቱ እርሱ ‹‹የሕማም ሰው ደዌንም የሚያውቅ›› እንደሆነ ትረዳላችሁ። (ኢሳ. $3.3) በግርግም ተወለደ ፣ በድህነት ኖረ ፣ መናቅንም ቀመሰ ፣ ሕይወቱ የትሕትናና የየዋህነት ነበር ፤ ይህን ያደረገውም ኩራታችንን ሊያጠፋ ፣ ትምክህታችንንና መታበያችንንም ሊያፈርስ ነው።

በማንኛውም ነገር በራስህ አትታመን ፤ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ‹‹ሌሎች ሁሉ ቢክዱህ እኔ ግን አልክድህም›› ብሎ በራሱ ባይተማመን ኖሮ አይወድቅም ነበር። (ማቴ. !6."3)

‹‹እኔም በደስታዬ። ለዘላለም አልታወክም አልሁ። አቤቱ፥ በፈቃድህ ለሕይወቴ ኃይልን ሰጠሃት ፊትህን መለስህ፥ እኔም ደነገጥሁ።›› (መዝ. ".6-7)

ቁሳዊም ሆነ መንፈሳዊ ሀብት ቢኖርህ ፣ ከፍ ያለ የበጎነት ደረጃ ቢኖርህ ፣ ሙት የማስነሣት ፣ አጋንንትን የማውጣት ፣ ሕሙማን የመፈወስ ጸጋ ቢኖርህ ራስህ ያመጣኸው ጸጋ አይደለምና ለራስህ አንድም ቦታ አትስጥ።

ልብህ ሲታበይና ሲመካ ቀጥሎ እንደምትወድቅና በጎ ነገሮችህ መውደቅ ምክንያቶችና የመዋረድህ መንሥኤ እንደሚሆኑ እወቅ።

አንተ ሰው! የአንተ የሆነ አንዳች ነገር ሳይኖር ለምን ትታበያለህ? ያለህ ነገር ሁሉ የእግዚአብሔር አይደለምን? በእግዚአብሔር ላይ ትታበያለህ? ‹‹በውኑ መጥረቢያ በሚቈርጥበት ሰው ላይ ይመካልን? ወይስ መጋዝ በሚስበው ላይ ይጓደዳልን? ይህስ፥ በትር የሚያነሣውን እንደ መነቅነቅ ዘንግም እንጨት ያይደለውን እንደ ማንሣት ያህል ነው።›› (ኢሳ. 0.05) አንተ በራሱ መንቀሳቀስ የማይችል በእግዚአብሔር እጅ ያለ በትር ነህ እንጂ ምንም አይደለህም። እርሱ ያንቀሳቅስሃል ፣ እንደ ወደደ መጠን ፣ በወደደበት ጊዜ ወደ ወደደው ይመራሃል።

የዓለምን ጠቢባንንስ ያሳፍር ዘንድ እግዚአብሔር የተናቁትንና አላዋቂዎችን አልመረጠምን?

‹‹ነገር ግን እግዚአብሔር ጥበበኞችን እንዲያሳፍር የዓለምን ሞኝ ነገር መረጠ፤ ብርቱንም ነገር እንዲያሳፍር እግዚአብሔር የዓለምን ደካማ ነገር መረጠ፤እግዚአብሔርም የሆነውን ነገር እንዲያጠፉ የዓለምን ምናምንቴ ነገር የተናቀውንም ነገር ያልሆነውንም ነገር መረጠ፥ ሥጋን የለበሰ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እንዳይመካ፡፡›› (1ቆሮ. 1.!7-!9)

‹‹አንዱ ምንም ሳይሆን ምንም የሆነ ቢመስለው ራሱን ያታልላልና፡፡›› ገላ. 6.3

‹‹ማንም አንዳች የሚያውቅ ቢመስለው ሊያውቅ እንደሚገባው ገና አላወቀም፤ ማንም ግን እግዚአብሔርን ቢወድ እርሱ በእርሱ ዘንድ የታወቀ ነው፡፡›› (1 ቆሮ. 8.2-3)

‹‹›በክርስቶስም በኩል ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ያለ እምነት አለን፡፡ ብቃታችን ከእግዚአብሔር ነው እንጂ፥ በገዛ እጃችን እንደሚሆን አንዳችን እንኳ ልናስብ ራሳችን የበቃን አይደለንም፤›› (2ቆሮ. 3.4-5)

# ከንቱ ውዳሴ

ከንቱ ውዳሴ የተደበቀ ክፋት ፣ የማይታይ ግብዝነት ፣ አደገኛ ወረረሽኝ ፣ በጎ ሥራን የሚያበላሽ ክፉ ትል ፣ በሐሰት ጭንብል እንድንታይ የሚያደርገን ተራ ትምክህት ፣ በእኛ ውስጥ በሌሉና በማናውቃቸው በጎነቶችና ጸጋዎች እንድንደሰት የሚያደርገንና ድክመቶቻችንን እንዳናይ የሚያሳውረን ነው፡፡

ከንቱ ውዳሴ መልካን ነገሮቻችንን ሁሉ የሚነጥቀን ፣ የድካማችንን ፍሬ ሁሉ የሚዘርፈን ወንበዴ ነው፡፡ የተወደድከው ሆይ! ከንቱ ውዳሴ በራስህ የመመካትህና የመኩራራትህ ማረጋገጫ ፣ የትምክህትህም ውጤት መሆኑን እወቅ!

አስተውል! በበጎነት መንገድ እየተጓዝህ እንኳን ቢሆን ከንቱ ውዳሴ ይህንን በጎነት ይነጥቅሃል፡፡ በወደብ ላይ ሆነህ እንኳን ያሰጥምሃል ፤ በደህና ስፍራ እያለህ እንኳን ይዘርፍሃል፡፡

በከንቱ ውዳሴ መያዝ መርከቡን በውድ ዕቃዎች እንደሞላ እና በመርከቡ ላይ ባለች ትንሽ ቀዳዳ ምክንያት ሙሉ ንብረቱ እንደሚወድምበትና እንደሚሰጥም ሰው መሆን ማለት ነው፡፡

አንድ ሰው ሲያመሰግንህ የወደቅህባቸውን ብዙ ኃጢአቶችና ስኅተቶችህን አስታውስ ፤ ይህ ራስህን የምትቆጣጠርበት መንገድ ነው ፤ እንዲህ ካደረግህ ራስህን እየቀረበልህ ላለው ምስጋና የማይገባ ሆኖ ታገኘዋለህ፡፡

በጎ ሥራ የሰው ምስጋናና ይሁንታ እንደማያፈልገው አስታውስ። ምክንያቱም ከንቱ ውዳሴ የእውነት ጠላት ፣ የተራ ፍላጎት ማስፈጸሚያ ፣ የግብዝነት ጓደኛ ፣ ሰዎችን ‹‹የከበሬታ ስፍራና የከበሬታ ወንበርን›› እንዲፈልጉ የሚገፋፋ ነው። (ማቴ. !3.6)

ከንቱ ውዳሴ ተናካሽ አውሬ ነው። በውስጡ የተቀመጡትን መልካም ነገሮች ጠብቆ ለማቆየት የማይችል የተሰበረ መርከብም ነው።

የከንቱ ውዳሴ ባለቤት የሆነ ሰው ሥራው እንደ ጢስ የሚተንን እንደ አየርም ተንኖ የሚቀር ነው። የከንቱ ውዳሴን መግቢያ ቀዳዳ እወቅ! በበጎ ሥራዎችህ ታገኝ የነበረውን ዋጋ ሁሉ የሚዘርፍህ ሌባ ነው። በሚዛን እስኪያቀምጥህና ስሜት አልባ እስኪያደርግህ ድረስ ነፍስህን ስለምንም ነገር እንዳታስብ የሚገፋፋት ነው።

ቅዱስ ጎርጎርዮስ እንዲህ ብሏል ፡- ‹‹ከንቱ ውዳሴ በመንገድህ ሁሉ የሚከተልህ የተሸሸገና ጭንብል ያጠለቀ ሌባ ነው። አሳዳጅህ በመሆኑ በጣም ደህንነት በሚሰማህ አሳቻ ሰዓት ሳታውቀው ይዘርፍሃል ፤ ይገድልህማል።››

ታላቁ ቅዱስ ባስልዮስ ደግሞ ‹‹ወዳጅ መሳይ ጠላታችን ነውና ሀብቶቻችንን ደስ በሚል መንገድ ይነጥቀናል።›› ብሏል።

እግዚአብሔር በመልካም ሥራዎች ካስጌጠህ በከንቱ ውዳሴ አትጣው ወይም አታበላሸው። በብዙ ጥረትና በትጋት

ያገኘውን ጽድቅ ያጣ አሳዛኝ ደሃ ትሆናለህ፡፡ ንጉሥ ሰሎሞን እንዳለው ‹‹ነፋስን እንደመከተል›› ይሆንብሃል፡፡ (መክ. 1.04) ሁሉን ነገር ለእግዚአብሔር ክብር በማድረግ ይህንን በሽታ አክመው፡፡

የምትሠራው ሥራ ዓላማ እግዚአብሔርን ከፍ ለማድረግ እና ደስ ለማሰኘት ይሁን፡፡ ‹‹ይህች እኔ በጉልበቴ ብርታት ለግርማዬ ክብር የመንግሥት መኖሪያ እንድትሆን ያሠራኋት ታላቂቱ ባቢሎን አይደለችምን? ›› እንዳለው እንደ ናቡከደነጾር ትዕቢተኛ አትሁን፡፡ (ዳን. 4.") ይልቅስ አንበሳ ገድሎ ለእናትና አባቱ እንዳልተናገረው እንደ ሶምሶን ሁን፡፡ (መሳ. 04.6)

ሰው ሲያመሰግንህ ስትሰማ ለእርሱ ብቻ ክብርን ልንሰጠው ለሚገባን ለእግዚአብሔር ክብርን ስጥ፡፡

የሳሙኤል እናት ሀና እንዲህ አለች ፡- ‹‹አትታበዩ፥ በኩራትም አትናገሩ እግዚአብሔር አዋቂ ነውና፥ እግዚአብሔርም ሥራውን የሚመዝን ነውና፥ ከአፋችሁ የኵራት ነገር አይውጣ፡፡ ከሕዝቡ መኳንንት ጋር ያስቀምጣቸው ዘንድ፥ የክብርንም ዙፋን ያወርሳቸው ዘንድ፥ ችግረኛውን ከመሬት ያስነሣል፥ ምስኪኑንም ከጉድፍ ያስነሣል›› (1ሳሙ. 2.3 ፣ 8)

ከከንቱ ውዳሴ የሚፈውስህ ወይም የሚጠብቅህ መድኃኒት ትፈልጋለህ? ከሠራኻቸው ሥራዎች ሁሉ በላይ የሆነውን የእግዚአብሔርን ክብር በመመልከት ላይ አተኩር፡፡ ትኩረትህ የጠራ በሆነ መጠን የአንተ ሥራ በእግዚአብሔር ፊት

የማይጠቅም ሆኖ ታገኘዋለህ። ‹‹የሰውነት መብራት ዓይን ናት። ዓይንህ እንግዲህ ጤናማ ብትሆን፥ ሰውነትህ ሁሉ ብሩህ ይሆናል፤ ዓይንህ ግን ታማሚ ብትሆን፥ ሰውነትህ ሁሉ የጨለመ ይሆናል።›› (ማቴ. 6.!2-!3) የምታይበት መንገድ መልካምነት ወሳኝ መሆኑንም ‹‹በኵራቱም ቅዱስ ከሆነ ብሆው ደግሞ ቅዱስ ነው፤ ሥሩም ቅዱስ ከሆነ ቅርንጫፎቹ ደግሞ ቅዱሳን ናቸው።››ሲል ያስረዳል። (ሮሜ. 01.06) ሥሩ ከተበላሸ ግን ፍሬን አትጠብቅ ይልቅስ ግንዱ ለእሳት ይሆናል።

ከዓለም ክብርን ሊያገኙ የሚሹ ሁሉ የእግዚአብሔር የሆነውን ክብር እንደሚሰርቅ እንደ ዲያቢሎስ ናቸው። ስለዚህ ሁልጊዜ ለእግዚአብሔር ክብርን መስጠትን አትዘንጋ። እንደተጻፈ :-

‹‹ብቻውን አምላክ ለሚሆን ለማይጠፋው ለማይታየውም ለዘመናት ንጉሥ ምስጋናና ክብር እስከ ዘላለም ድረስ ይሁን፤ አሜን።›› 1ጢሞ. 1.07

‹‹እኔ እግዚአብሔር ነኝ ስሜ ይህ ነው ክብሬን ለሌላ … አልሰጥም።›› ኢሳ. #2.8

‹‹ለእኛ አይደለም፥ አቤቱ፥ ለእኛ አይደለም፥ ነገር ግን ለስምህ ስለ ምሕረትህ ስለ እውነትህም ምስጋናን ስጥ።›› መዝ. )05.1

‹‹እንግዲህ የምትበሉ ወይም የምትጠጡ ብትሆኑ ወይም ማናቸውን ነገር ብታደርጉ ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት፡፡›› 1ቆሮ. 0.''1

‹‹ማንም ሰው የሚናገር ቢሆን፥ እንደ እግዚአብሔር ቃል ይናገር፤ የሚያገለግልም ቢሆን፥ እግዚአብሔር በሚሰጠኝ ኃይል ነው ብሎ ያገልግል፤ ክብርና ሥልጣን እስከ ዘላለም ድረስ ለእርሱ በሚሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር በነገር ሁሉ ይከብር ዘንድ፤ አሜን፡፡›› 1ቆሮ. 4.01

ስለዚህ ሰዎችን ረድተህ ፣ ተንከባክበህ ወይም አገልግለህ ከሆነ ወይም መልካም ነገር አድርገህላቸው ከሆነ ሁሉንም ለእግዚአብሔር ክብር አድርገው፡፡ ‹‹ለሰው ሳይሆን ለጌታ›› (ኤፌ. 6.7)

# ራስን ማመስገን አይገባም!

‹‹ሌላ ያመስግንህ እንጂ አፍህ አይደለም ባዕድ ሰው እንጂ ከንፈርህ አይደለም፡፡›› (ምሳ. !7.2)

‹‹ብዙ ማር መብላት መልካም አይደለም እንዲሁም የራስን ክብር መፈላለግ አያስከብርም፡፡›› (ምሳ. !5.!7)

ድክመቶቹን ሳይገልጽ ስለ መልካም ሥራዎቹ የሚኮራና ምስጋናን የሚቀበል ሰው ንጹሕ የሆነውን ደሙን እያፈሰሰ የተበከለውን ደም በሰውነቱ የሚያቆይ ሰው ይመስላል፡፡ ለራስህ ክብርን ለመስጠት ራስህን የምታመሰግን ሆይ! በጎ ሥራዎችህን በማሳወቅህ ሰዎች የበለጠ የሚወድዱህ ይመስልሃል? እኔ ግን የምነግርህ ዜና አለኝ ፤ ራስህን ከፍ ከፍ በማድረግህ ምክንያት ሰዎች ይንቁሃል ፤ ያቃልሉሃል፡፡ ጤነኛ ነህ ብለው ካሰቡ ደግሞ እንዳልበሰልህና እምነት የሚጣልበት ሰው እንዳልሆንህ አድርገው ይገምቱሃል፡፡ ስለዚህ በጎ ሥራህን ደብቅ ፣ የደጉ ሣምራዊ ተግባሮችህንም ሁሉ ሸፍናቸው ፤ ከሌሎች የተሸልህ እንደሆንህ ለማሳወቅና ፍንጭ ለመስጠት አንዲትም ቃል አትናገር፡፡ ምክንያቱም በእግዚአብሔርና በሰዎች ፊት ልትኩራራ አይገባህም፡፡ እንደተጻፈው ፡-

‹‹ፈሪሳዊም ቆሞ በልቡ ይህን ሲጸልይ፡፡ እግዚአብሔር ሆይ፥ እንደ ሌላ ሰው ሁሉ፥ ቀማኞችና ዓመፀኞች አመንዝሮችም፥ ወይም እንደዚህ ቀራጭ ስላልሆንሁ አመሰግንሃለሁ፤ በየሳምንቱ

ሁለት ጊዜ እጦማለሁ፥ ከማገኘውም ሁሉ አሥራት አወጣለሁ አለ።›› (ሉቃ. 8.01-04)

‹‹ብዙ ሰዎች ቸርነታቸውን ያወራሉ የታመነውን ሰው ግን ማን ያገኘዋል?... ልቤን አነጻሁ፥ ከኃጢአትም ጠራሁ የሚል ማን ነው?›› (ምሳ. !.6 ፣9)

‹‹ማንም ለሰርግ ቢጠራህ በከበሬታ ስፍራ አትቀመጥ፤ ምናልባት ከአንተ ይልቅ የከበረ ተጠርቶ ይሆናልና አንተን እርሱንም የጠራ መጥቶ። ለዚህ ስፍራ ተውለት ይልሃል፥ በዚያን ጊዜም እያፈርህ በዝቅተኛው ስፍራ ልትሆን ትጀምራለህ። ነገር ግን በተጠራህ ጊዜ፥ የጠራህ መጥቶ። ወዳጄ ሆይ፥ ወደ ላይ ውጣ እንዲልህ፥ ሄደህ በዝቅተኛው ስፍራ ተቀመጥ፤ ያን ጊዜም ከአንተ ጋር በተቀመጡት ሁሉ ፊት ክብር ይሆንልሃል። ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳልና፥ ራሱንም የሚያዋርድ ከፍ ይላል።›› (ሉቃ.04.8-01)

‹‹በንጉሥ ፊት አትመካ፥ በታላልቆችም ስፍራ አትቁም ፤ ዓይኖችህ ባዩት በመኰንን ፊት ከምትዋረድ። ወደዚህ ከፍ በል ብትባል ይሻልሃልና።›› ምሳ. !5.6-7

‹‹ሰውን ትዕቢቱ ያዋርደዋል መንፈሱን የሚያዋርድ ግን ክብርን ይቀበላል።›› ምሳ. !9.!3

# በማንነትህ አትታበይ!

በማንነትህ ወይም በከበሩ ቤተሰቦችህ ወይም ዘር ማንዘሮችህ አትታበይ፡፡ አንተ መልካም አድራጊ ካልሆንህ ከከበሩ መልካም ሰዎች ጋር መዛመድህ ወይም ባለ ደረጃ መሆንህ ምን መልካምን ነገር ሊያደርግልህ ይችላል?

የዘመዶችህ ክብር በራሱ ወይም ብቻውን እውነተኛ ክብር ነው እንበል፡፡ የቅድመ አያቶችህና የመሠረቶችህን ክብራቸውን ማየት ትፈልጋልህ? መቃብራቸውን ክፈት ፤ የአጥንቶቻቸውን ቅሪቶች ፣ ስብርባሪዎች ታገኛለህ፡፡ ይህስ ያኮራህ ይሆን? ጻድቁ ኢዮብ እንዲህ ብሏል ፡- ‹‹ተስፋ ባደርግ ሲኦል ቤቴ ናት ምንጣፌንም በጨለማ ዘርግቻለሁ፡፡መበስበስን፦ አንተ አባቴ ነህ ትልንም፡፡ አንቺ እናቴ እኅቴም ነሽ ብያለሁ፡፡›› (ኢዮ. 07.03-04) ከባለጸጎች ፣ የተከበሩና ከዝነኞች ቤተሰብ ተገኝተህ ተስፋ ቢስ፣ የመልካምነትና የሥነ ምግባር ደሃ ከምትሆን ይልቅ የተራ ሰው የልጅ ልጅ የደሃም ሰው ልጅ ሆነህ ጻድቅና መልካም ሰው ብትሆን ይሻልሃል፡፡

ቤተሰቦችህ የከበሩና ትልቅ ደረጃ ላይ ያሉ ሆነው አንተ ክፉና ወራዳ ከሆንህ ከዘመዶችህ ያገኘሽውን መሠረት እያፈረስህ ነው፡፡ ጻድቅ የሆነና ራሱን ቀስ በቀስ ለክብር ያበቃ ሰው ክብን አግኝቶ ከሚያጣው ሰው ይሻላል፡፡ ይህንን ያገኘሽውን ክብር

መጠበቅና ማቆየት ካልቻልህ የከበሩ ዘመዶችህ ምን ሊያደርጉልህ ይችላሉ? አንድ ቁምነገር ማወቅ ትፈልጋለህ? ግን እንዳቆጣ! በዘመድ አዝማድ መመካት አንድን ነገር ያረጋግጣል ፤ አንተ ምስኪን ፣ ችግረኛና ደሃ መሆንህን!! የአንተ ያልሆነውን የሌሎችን ንብረት ለመጠቀም እንደምትፈልግ ፣ ዕርቃንህን የሆንህና የሌሎችን ልብስ ለብሰህ ማጌጥ የምትፈልግ መሆንህን የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህ ትጠቀማለህ በሚለው ነገር እጠራጠራለሁ ፤ ምክንያቱም የተዋስኸው ነገር የአንተ አይደለማ! አንተን የሚመስሉ ሰዎች የሌሎችን በጎነት የሚያሳዩና የራሳቸውን ስኅተት የሚያውጁ ናቸው፡፡ የአንተ ክብር በመልካምነትህ እንጂ በዘሮችህ ፣ በሥራህ እንጂ በዝምድናህ አይደለም፡፡

አይሁድ የአብርሃም ዘርና ዘመዶች በመሆናቸው ሲኮሩ መድኃኔዓለም እንዲህ አላቸው፡፡ ‹‹ኢየሱስም፦ የአብሃም ልጆች ብትሆኑ የአብርሃምን ሥራ ባደረጋችሁ ነበር፡፡›› (ዮሐ. 8."9) አንተም ከከበሩ ወገኖችህ ጋር መታሰብ ከፈለግህ ለእነርሱ ደረጃና ክብር የሚመጥን ነገር በማድረግ ስማቸውን ጠብቅ ፤ የእነርሱን ጎዳና ተከተል ፤ በመንገዳቸውም ላይ ሒድ፡፡

ዳዊት ከድሆች ወገን ነበረ፤ በጎነቱና ጻድቅነቱ ግን ከፍ ያሉ ክብርን ይገነቡለት ስለነበር የከበረ አደረጉት፡፡ የነገሥታት ልጅ የነበረው ክፋው ንጉሥ አክአብስ ምን አደረገ? እርሱ በኤልያስ ዘመን የሰሜናዊው የእስራኤል ግዛት ንጉሥ ነበረ ፤ ለሃይማኖታዊ ብጥብጥ ፣ የናቡቴን ርስት ቀምቶም ለመግደሉ

ምክንያት የሆነችውን ሲዶናዊቷን ልዕልት ኤልዛቤልን አገባ፡፡ (1ነገሥ.06.!9)

በጭቃ እስከተበከለ ድረስ ከትቦው ንጹሕ ሆኖ የተለቀቀ ውኃ ምን ይጠቅማል?

ኢየሩሳሌምን ሲገሥጽ ነቢዩ ሕዝቅኤል እንዲህ አለ ፡- ‹‹አባትሽ አሞራዊ ነበረ እናትሽም ኬጢያዊት ነበረች፡፡›› (ሕዝ. 06.3) አምሮታቸውን እና ፍትወታቸውን ስለተከተሉ እንጂ በዘሮቻቸው እንዳልሆነም ነገራቸው፡፡

ሌሎችን ከደሃ ወይም ከዝቅተኛ ደረጃ ካው ቤተሰብ በመገኘታቸው እየናቅህ ከከበሩ ሰዎች ወገን በመሆንህ አትመካ፡፡ ሁላችን ከአንድ አባት አይደለንምን? እርሱ ክቡር ከሆነ ሁላችንም የከበርን ነን ፤ እርሱ ምስኪን ከሆነም እኛም እንዲሁ እንሆን ነበር፡፡

የሰማያዊው ንጉሥ የእግዚአብሔር ልጆች በመሆናችን ምክንያት የከበርን ነን፡፡ በፍቅርም ወደ እርሱ ‹‹አባታችን ሆይ!›› ብለን እንጣራለን፡፡ ለአንዳችን ሳይሆን ለሁላችንም አባት ነው፡፡ የከበሩ ዘሮቼ ነኝ ካልህ ግን ‹‹እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ፡፡›› ከተባሉት ትሆናህ፡፡ (ዮሐ. 8.#4)

ከድሃ ወላጆች መገኘት ለአንድ ሰው ኀስቋላነት ምክንያት ሊሆን አይችልም ፤ ምክንያቱም ማንም ሰው የሚወለድበትን ቤተሰብ መርጦ ሊወለድ አይችልም፡፡ ስለዚህ እንዲህ ያለውን

ሰው በጎና ጻድቅ መሆኑን አስበህ አትናቀው ፤ አክብረው ፣ እንደራስህ አድርገህ ቁጠረው። ንጉሥ ፣ ባለሥልጣን ፣ ባለጸጋ ብትሆንም ሰው መሆንህን እወቅ! ደሃውም ሰው ልክ እንዳንተ ያለ ሰው ነው። ደስ ከሚያሰኙ ሥዕሎችህና ከሚጠፉት ነገሮችህ በቀር እንደ አንተ ነው።

እግዚአብሔር ሳኦልን ከታናሽ የእስራኤል ጎሣዎች ለእስራኤል ንጉሥ አድርጎ መርጦታል። የጋለሞታይቱ ልጅ የነበረውን ገለዓዳዊውን ዮፍታሔንም እስራኤልን እንዲመራና ከአሞናውያን እጅ እንዲያድናቸው መርጦታል። (መሳ. 01)

እንዲሁም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱን የመረጠው ከልዑላን ፣ ከከበሩ ሰዎች መካከል ሳይሆን ከአሣ አጥማጆች ፣ ካልተማሩ ሰዎችና ከምስኪኖች መካከል ነው ፤ ጠቢባንና ባለጸጎችን አልመረጠም።

# በኃይልና ጥንካሬህ አትታበይ!

እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፡- ‹‹ዓለሙን ስለ ክፋታቸው ክፉዎቹንም ስለ በደላቸው እቀጣለሁ የትዕቢተኞችንም ኵራት አዋርዳለሁ።›› የቱንም ያህል ኃያል ብትሆን አትታበይ ፣ አትመካ ፣ በኃያልነትህም አትፎክር። ምክንያቱም እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ያዋርዳል ፣ የሚኮሩትንም ዝቅ ያደርጋል። በኃይሉና በስልጣኑ የተመካውን ጎልያድን ተመልከት! በእጁ አንድም ሰይፍ ያልያዘው ትንሹ ዳዊት በእግዚአብሔር ኃይል በገዛ ሰይፉ አንገቱን ቆርጦታል።

‹‹ንጉሥ በሠራዊቱ ብዛት አይድንም ኃያልም በኃይሉ ብዛት አያመልጥም።›› (መዝ."3.!6)

‹‹በቀስቴ የምታመን አይደለሁምና፥ ሰይፌም አያድነኝምና›› መዝ. #4.6

‹‹ከኃይል ይልቅ ጥበብ ይሻላል ፤ ጠቢብም ከጉልበተኛ ይሻላል።›› ጥበ. 6.1

የነፍስ ክብር እውነተኛ ኃይልና ትክክለኛ ጥንካሬ ነው። ይህ ጥንካሬ አንዳች ክፉ ነገር እንዳያስፈራን የሚያደርግና ብዙ መከራና ሥቃይን ለመቋቋም የሚያስችል ነው። ይህ እውነተኛ ጥንካሬ ሌላ ጥንካሬ ሊተካከለው የማይችል ነው።

የቱንም ያህል ጠንካራና ኃይለኛ ብትሆን ልትመካ አይገባም ምክንያቱም ይህን ጥንካሬ እግዚአብሔር ለእንስሳትም ሰጥቶአቸዋል፡፡ የነፍስ ጥንካሬ ግን እውነተኛ ክብር ነው፡፡ ሰዎች በአንተ ላይ የሚናገሩትን ትንሽ ክፉ ቃል በመስማት የምትረበሽ ከሆነ እንዴት ነፍስ ጥንካሬ እንዲኖርህ ትጠብቃለህ?

እውነተኛ ጠንካራ ከሆንክ ከባድ ችግርና ጥቃቶች ሲደርሱብህ አትታወክም፡፡ እንዲያውም ችግር ያደረሰብህን ሰው ይቅር ትላለህ፡፡ ችግር በሚደርስብህ ጊዜ የምትረበሽና ራስህን መግዛት የማትችል ከሆነ ግን ደካማና ራሱን መግዛት የማይችል ነህ ማለት ነው፡፡ በምኞትና በሕመም ከመሸነፍ በቀር ደካማነት የለም፡፡

ክብርህና ጥንካሬህ ወዴት አለ? የረከሰ ምኞትህ ድል የሚነሣህ ከሆነ ዕብሪትህ ፣ ኃይልህና ጥንካሬህ የት ድረስ ያደርስህ ይሆን? ጠንካራና ኃያል ከሆንክስ ጠላት ሳያሸንፍህ በፊት እስቲ መቃብርን አሸንፍ ሞትንም ድል አድርግ፡፡ አንተ ዕብሪተኛ ሆይ! ጠንካራነትህን እያሳየህ አይደለህም፡፡ ነገር ግን ይህ ሁሉ ትምክህትህ ከንቱ መሆኑን ፣ እውነተኛውን የነፍስ ጥንካሬና የሚሰጠውን ውስጣዊ ክብር ዕወቅ፡፡

ኃጢአትን መቋቋም ከቻልህ ትልቅ ኃይል አለህ፡፡ .... ክፉ ሀሳቦችን መግደል የቻሉ የድል አክሊልን ሊጎናጸፉ የሚገባቸው ድል አድራጊዎችና ጀግኖች ናቸው፡፡

# ሥጋዊ ውበትን ጠናቅ

ጠቢቡ እንዲህ ብሎ ነበር ፤ ‹‹ውበት ሐሰት ነው ፤ ደም ግባትም ከንቱ ነው›› (ምሳ. "1.") ብዙ ነገሮች ከውበታቸውና ከማራኪነታቸው የተነሣ የፈጠራቸውን አምላክ ክብር ይናገራሉ። ነገር ግን ብዙ ሰዎች በዚህ የተፈጥሮ ውበት ቢደነቁም ስለ ድንቅ ፍጥረቱ ለእግዚአብሔር ክብርን አይሰጡም። እንዴት ያሳዝናል? የአቤሴሎም የጸጉሩ ውበትና ገጽታው ለሞቱ ምክንያት ነበረ። (2ሳሙ. 08)

ሕጻናት ውብ ሥዕል ተሰቅሎ ሲያዩ በጣም ይሳባሉ ፣ ለጥቂት ጊዜም አንጋጥጠው በማየት ይቆያሉ። አንተ ግን ውበትን ባየህ ቁጥር እንደ ሕጻናት ቆመህ የምታይ አትሁን። ይልቁንስ በዚያ ውበት ውስጥ ያለውን ትልቅ ትምህርት አስተውል ፤ ያን ጊዜ የፈጣሪን ታላቅነትና እርሱ የፈጠራቸው ነገሮች የውበት ዳርቻ እንደሆኑ ትረዳለህ። አንተ እያየኸው ያለኸው ውብ ነገርም የማይመረመረው ከፈጣሪ ውበት የተገኘ በውቅያኖስ ውስጥ እንዳለ ጠብታ መሆኑንም አስታውስ።

በሥጋዊ ውበት አትማረክ ፤ ይልቅስ ውስጣዊውን የነፍስ ውበት በመመርመር የሥጋን ውበት ከመንፈስ ውበት ለይ። የምትረዳው ነገር ሥጋ የትሎች ምግብ መሆኑንና የሚበሰብስና ሽታን የሚያመጣ መሆኑን ነው። ውጪውን አትመልከት ፤ ውስጣዊውን ማንነት የሚቆጣጠረውን ውስጠኛውን ተመልከት

እንጂ፡፡ በውጪያዊ ውበት አትማረክ ፤ ምክንያቱም ውጪያዊው ውበት ከንቱ ነው ፣ ውጪያዊ ውበትን የጊዜ ብዛት ያደበዝዘዋል ፣በሽታ ያበላሸዋል ፣ ውሎ አድሮም ይሞታል፡፡ እጅግ የሚማርክ ውብና ብርቱ የሆነ ሰውነት በትሎችና በምስጦች ሲበላ አይተሃል? ይህ አስደናቂና ማራኪ ሰው አንድ ቀን አንደበቱ ተይዞ ይሞታል ብለህ ትገምት ነበር? እነዚያ ማራኪ ዓይኖችስ ወደ ተፈጠሩበት መሬት ተመልሰው ትቢያ ይሆናሉ ብለህ ትገምት ነበር? (ዘፍ. 3.09)

‹‹ሥጋ ለባሽ ሁሉ ሣር ነው፥ ክብሩም ሁሉ እንደ ምድረ በዳ አበባ ነው፡፡የእግዚአብሔር እስትንፋስ ይነፍስበታልና ሣሩ ይደርቃል አበባውም ይረግፋል በእውነት ሕዝቡ ሣር ነው፡፡›› ኢሳ. #.6-7

የወጣትነት ውበት በዕድሜ ብዛት ይከስማል፡፡ እውነተኛው ውበት ግን አይከስምም ፣ አይሞትምም፡፡ የማይደበዝዝ ፣ የማይለወጥና በሞት የማይጠፋ ነው፡፡ ይህ እውነተኛ ውበት የሚገኘው በእግዚአብሔር አርአያ እና አምሳል በተፈጠረችው የማትሞት ነፍስ ውስጥ ብቻ ነው፡፡ (ዘፍ. 2.!6-!7)

ሌላ ውበት ይደበዝዛል ፤ ደም ግባትም ሁሉ ያልፋል፡፡ ነፍስ ስለ ውስጣዊ ውበቷ መጨነቅ ስትጀምር በዙሪያዋ ባሉ ፍጡራን ላይ ያለውን ውበት ትንቃለች፡፡

በዙሪያህ ያሉትን ፍጥረታትና አስደናቂ ነገሮች ሁሉ ልታይ ትችላለህ ፤ ከአንተ ነፍስ በስተቀር በእግዚአብሔር

አርኣያና አምሳል የተፈጠረ አንድም የለም፡፡ የተወደድኸው ሆይ እግዚአብሔር ለአንተ ከኅሊና በላይ የሆነውን የመጨረሻውን ውበት አጎናጽፎሃል!!

እውነተኛውን ውበት የምትፈልግ ከሆነ ራስህን በበጎነትና በክርስቲያናዊ አኗኗር አስጊጠው፡፡ ክፉ ነገሮችን በማየትና በመጥፎ ጠባይ አትቆሽሽ፡፡ ምናልባት አንድን ሰው ውብና ማራኪ ሆኖ ታየው ይሆናል፡፡ ነፍሱ ግን በክፋት ውስጥ ሰጥማለች ፣ በውስጡ ግን በኃጢአት እየታወከ ነው ፤ በብዙ ጥፋቶች ጥላሸትም ጠቁሮአል፡፡ በአንጻሩ የሚማርክ ገጽታ የሌለው ሰው ልታይ ትችላለህ ፤ ነፍሱ ግን በበጎነት እና በቅድስና አኗኗር የተዋበች ልትሆን ትችላለች፡፡ ስለዚህ እባክህን ሁልጊዜ ውስጣዊ ማንነትን መርምር እንጂ ውጪያዊ ውበትን አትመልከት፡፡

**‹‹ነገር ግን በክርስቶስ ሁልጊዜ ድል በመንሣቱ ለሚያዞረን በእኛም በየስፍራው ሁሉ የእውቀቱን ሽታ ለሚገልጥ ለአምላክ ምስጋና ይሁን!››** 2ቆሮ. 2.04